5

# አፄ ምኒልክ

# እና

# የአድዋ ድል

The Battle of Adwa

AFRICAN VICTORY IN THE AGE OF EMPIRE

Raymond Jonas

በሬይሞንድ ጆናስ

ትርጉም፡- ሙሉቀን ታሪኩ

© የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ ዕትም ፡- ጥቅምት 2006 ዓ.ም.
ሁለተኛ ዕትም፡- ኅዳር 2006 ዓ.ም

**ዋና አከፋፋይ**

**ዩኒቲ መጻሕፍት መደብር**

ከሰም ሆቴል ወደ ሾላ በሚወስደው መንገድ

ከሰም ሆቴል 100 ሜትር ከፍ ብሎ

ስልክ፡- 0912 028 794

፡- 0911 669 946

የመ.ሳ.ቁ. 4143

# ማውጫ

| ርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 11 |
| **ክፍል አንድ** | |
| **የአድዋ መንገድ** | |
| ምዕራፍ አንድ፡- የንጉሥ ህልም | 19 |
| በቴዎድሮስ ላይ የተደረገው ዘመቻ፡- የወረራ ቅድመ ሁኔታ | 24 |
| የግብፅ በኢትዮጵያ ላይ መነሣት | 29 |
| የኢትዮጵያ የምንግዜም ኃይለኛ ጥንዶች-ምኒልክ እና ጣይቱ | 32 |
| ምዕራፍ ኹለት፡- ከአድዋ አቅራቢያ | 36 |
| ምፅዋዕ፡- የዘመናት ግዛተ-አፄዎች ማዕከል | 40 |
| ምዕራፍ ሦስት፡- ጣሊያን በአፍሪካ | 45 |
| የግብፅ በር ከፋችነት እና የጣሊያን አገባብ | 49 |
| የጣሊያን ወደ ተራራማው የኢትዮጵያ ግዛት መጠጋት | 50 |
| ምዕራፍ አራት፡- የነፃነት ዋጋ | 62 |
| ምኒልክ ወደ ወላይታ ያደረጉት ዘመቻ | 65 |
| የምኒልክ ዘመቻ በውጪው አለም እይታ | 70 |
| ምዕራፍ አምስት፡- የነጭ ቅጥረኛ ጥቁሮች | 73 |
| የባንዳ ባታሊዮኖችን ማደራጀት | 74 |
| ፍቅር በአፍሪካ | 79 |

ምዕራፍ ስድስት፡- አፍሪካ በጣሊያን 84
የሐረር አሥተዳዳሪው መኮንን 90
የራስ መኮንን የጣሊያን ተልዕኮ 97
"የግራማዊነትዎ ጥበቃ እንዲደረግልኝ እጠይቃለሁ" 101
ምዕራፍ ሰባት፡- "ለአገሬ ውርደት" 106
የኤርትራ አፈጣጠር 109
የሰፈራ ቅኝ ግዛት በኤርትራ 113
ባሕታ ሃጎስ እና ልዑል መንገሻ፡- ከነጭ እባብ ጋር የተደረገ ግብ ግብ 117
ባራቴሪ የኢትዮጵያን ድንበር ጣሰ 121

## ክፍል ኹለት

## የአድዋ የጦር ሜዳ ውሎ

ምዕራፍ ስምንት፡- የምኒልክ ዘመቻ 124
ሕዝባዊ ቅስቀሳ በኢትዮጵያ 125
የዘመቻው አጀማመር 128
ምዕራፍ ዘጠኝ፡- አምባ'ላጌ 132
የጣሊያን ክቅዠቷ መባነን 135
ታሪክ የቀየረው የአምባ'ላጌ ውሎ 139
የመቀሌው ምሽግ 142
የበዓለ-ጥምቀት ስልፍ 145
የተራበ የይሁዳ አንበሳ ሲሳይ 150



ቀድመው ምኒልክ እና ጣይቱ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻቸውን በአውሮፓ አጧጡፈው ነበር።

ከ1878 ጀምሮ አፄ ምኒልክ ከአውሮፓ ጋር ኹለንተናዊ ግንኙነት የሚያደርጉት በአማካሪያቸው ስዊዘርላንዳዊው መሐንዲስ አልፍሬድ ኢልግ በመታገዝ ነበር። በ1890ዎቹ ንጉሡ ኢልግን በተደጋጋሚ ወደ አውሮፓ በመላክ የራሳቸውንና የአገራቸውን ገጽታ ለመገንባት ችለዋል። ኢልግም በተልዕኮው ተራራማውን የኢትዮጵያ መልክዐ ምድር የሚያሳይ ፖስት ካርድ «የአፍሪካዋ ስዊዘርላንድ›› ከሚል ጽሑፍ ጋር በማያያዝ ኢትዮጵያን ከአውሮፓውያኑ ጋር የበለጠ አስተዋውቋል። በተጨማሪም የምኒልክን ዘውዳዊ ምስል የያዙ ፖስት ካርዶች፣ የመዝበያ ሳንቲሞች፣ የፖስታ ቴምብሮች እና ማኅተሞች በአውሮፓ በማሠራጨት የንጉሡን ሉዐላዊነት ቀድሞ አስተዋውቋል።

በኢልግ በተጨማሪ ተጓኘ ጋዜጠኛ የነበረው ካዝሚር ምንዶን-ቪዳል ሄት በ1982 ጀምሮ በተለያዩ የአውሮፓ የኅትመት ውጤቶች ላይ ስለ ምኒልክ እና ኢትዮጵያ በመጻፍ ጉልህ የማስተዋወቅ ሥራን ሠርቷል። የሞንዶን-ቪዳልሔት ጽሑፎች ምኒልክን በጉልህ ያስተዋወቀ ሲኾን የንጉሡን ግዛት ከመካከለኛው ዘመን የአውሮፓ ነገሥታት ጋር በማነፃፀር እንዲህ ጽፎ ነበር፡- «የኢትዮጵያን ንጉሣዊ ግዛት- አፄ ስመለከት የእኛ የአውሮፓውያን የመካከለኛው ዘመን ነገሥታት ከመቃብር ወጥተው በኢትዮጵያ ተራሮች የተሸሸጉ ያህል ይሰማኛል።›› የእርሱ ዘመን ኢትዮጵያ ከዘመናዊው አውሮፓ ጋር የሚያመሳስላት የዕድገት መስመር ላይ እንደምትገኝ በተደጋጋሚ ጽፏል።

የሞንዶን ጽሑፎች ምኒልክን ከክርስትና ዕምነት ጋር በማያያዝ ለአውሮፓ አስተዋውቀዋል። ምኒልክ በሙስሊም ጎረቤቶቻቸው ላይ ያለውን የበላይነት በማጋነን የጻፈ ሲሆን ምኒልክ በሙስሊሙ የወላይታ ግዛት ላይ ያስመዘገቡት ድል «መስቀል በጨረቃ ላይ የበላይነቱን ያረጋገጠበት›› በማለት ገልጿል። በአጠቃላይ ጣሊያን

ኢትዮጵያን ለመውረር በዝግጅት ላይ በነበረችበት ወቅት ሞንዶን በጽሑፎቹ ከኢትዮጵያ ጎን ቆሞ ነበር።

ከወረራው በፊት ሞንዶን ስለ ምኒልክ እንዲህ ጽፎ ነበር፦ «የኢትዮጵያው ንጉሠ-ነገሥት የአውሮፓ ሕዝቦችን አስተሳሰብ ያውቃል። ምክንያቱም የክርስቲያን ሕዝቦችን አመለካከት እና የፍትሕን ሥርዓት ያውቃል።» በአውሮፓ የተሠራጨው የምኒልክ ምስል ንጉሡ አንገቱ ላይ መስቀል አስረው ያሳይ ነበር። ይህ ደግሞ በአንድ አፍሪካዊ ንጉሥ ላይ ታይቶ አይታወቅም ነገር። በዚህም የተነሣ በርካታ የአውሮፓ ጋዜጦች የምኒልክን ምስል «የአፍሪካ ክርስቲያናዊ ንጉሥ» ከሚል የግርጌ ማስታወሻ ጋር ነበር የሚያወጡት።

በተለያዩ መንገዶች ምኒልክ እና ጣይቱ በመላው አውሮፓ እና በአሜሪካ ታዋቂ ሆነዋል። በምዕተ-ዓመቱ መባቻ የፓሪሱ ሙሴ ግሬቪን በሙዚዩም ለጣይቱ እና ምኒልክ የሰም ሐውልት አቁሞላቸዋል። በተመሳሳይም በቫኒቲ ፌይር የምኒልክ ሃውልት ቻርልስ ዳርዊን እና ቤንጃሚን ዲዝራኤል ሐውልት ጎን ተቀምጦ ነበር። ፌሊክስ ፖቲን የተባለ ባለ መደብር ደግሞ ለእያንዳንዱ ጎብኚ የአፄ ምኒልክ እና የጣይቱን ምስል የያዘ ፖስት ካርድ በስጦታ መልክ ይሰጥ ነበር።

የአድዋ ድል በበርካቶች ሕይወት ላይ አሉታዊ ጣጣ አስከትሎ ነበር። ጣሊያን በጦርነቱ ሽንፈትን ባስተናገደች ማግስት በጣሊያን የፍራንሲስኮ ክሪስፒ አስተዳደር የወደቀ ሲሆን የክሪስፒም ሥልጣን አክትሟል። የጣሊያንን ጦር የመራው ጀነራል አሬስቴ ባራቴሪ ከጦርነቱ ቢተርፍም ወደ አገሩ ተመልሶ ከመግባቱ በፊት ነበር ክስ ተመሥርቶበት ጉዳዩ በፍርድ ቤት መታየት የጀመረው። የባራቴሪ የክስ ታሪክ በተለያዩ የጣሊያን ተውኔቶች ላይ ክህደትን፣ ሽንፈትንና የዘር ልዩነትን ለማሳየት ይጠቀስ ነበር።

ከጦርነቱ በኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጣሊያናውያን በምርኮ የተያዙ ሲሆን ከስተቱም ግዙፍ ቁጥር ያለው የነጭ ሠራዊት በጥቁሮች እጅ ላይ የወደቀበት





የመጀመሪያ ታሪክ ሆኖ ተመዝግቧል። ለአንድ ዓመት ያህል በኢትዮጵያውያን እጅ ላይ የከረሙት ምርኮኞች በተደረገላቸው እንክብካቤ እና ኢትዮጵያውያኑ ባሳዩዋቸው ፍቅር ተገርመው ነበር። አብዛኞቹ ምርኮኞቹ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ጥብቅ ወዳጅነት የመሠረቱ ሲሆን የተወሰኑት በትዳር የተሣሠሩ እንደነበሩ ከማስታወሻዎች ላይ ለመረዳት ተችሏል። የእሥረኞቹን አያያዝ በተመለከተ ከራሳቸው ከምርኮኞቹ በተጨማሪ በወቅቱ በተለያየ ሥራ ላይ ተሰማርተው ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የግሪክ፣ የአርመንያ፣ የአይሁድ እና የስዊዘርላንድ ዜጎች በሰፊው ጽፈዋል።

ኢትዮጵያ ላይ የተቃጣው የወረራ ሙከራ ከኢምፔሪያሊዝም መስፋፋት መርሆዎች ያፈነገጠ ነበር። በኢትዮጵያ ለሰፈራ ቅኝ ግዛት የሚመች ሁኔታ አልነበረም፤ የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ለመሆን እንዲሁም የኢምፔሪያሊስት አውሮፓን ምርቶች ለመቀበል አመቺ የሆነ ገበያ አልነበራትም። የጣሊያን ቡርዧ መንግሥት «የጣሊያን ምሥራቅ አፍሪካ» ለመገንባት በነበረው ቀቢፀ ተስፋ ተገፋፍቶ ነበር ኢትዮጵያን የወረረው። ኮርየሬ ዴላ ሴራ የተባለው የሚላን ጋዜጣ የጣሊያን ፖለቲከኞች ታላቅ ግዛታቸውን በአፍሪካ እንዲገነቡ በማነሳሳት ይታወቅ ነበር። በተስፋፊነት ሕልም በመገፋፋት ነበር የጣሊያን መንግሥት በአገሩ የነበረውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ችላ በማለት በርካታ ገንዘብ በማውጣት ወደ ወረራ የገባው።

ኢትዮጵያን ሳያስገብር የከሸፈው የጣሊያን የወረራ ሙከራ ለየትኛውም ተስፋፊ ኢምፔሪያሊስት ትምህርት ሰጥቷል። በተለይም ሌሎች ሕዝቦችን በመናቅ ለመበዝበዝ የሚነሱ ወራሪዎች ትምህርት አግኝተውበታል። ጣሊያን ብቸኛዋ ምሳሌ አይደለችም። በርካታ መንግሥታት ለዘመናት ሲስፋፉና ሌሎችን ሲያስገብሩ ኖረዋል። በእርግጥ መነሻቸው የተለየ ቢሆንም። መንግሥታት ጥሬ ዕቃ ለማግኘት፣ ለምርቶቻቸው ገበያ ፍለጋ፣ ለዜጎቻቸው ሥራ ለመፍጠር፣ እና ለመሳሰሉት ዓላማዎች ሌሎችን ሲወሩ ኖረዋል። ጥቂት የማይባሉ ወራሪዎች የመንግሥታቸውን እና የግዛታቸውን ኃያልነት ለማሳየት ሲሉ ብቻ ወረራ የፈጸሙባቸውን ሁኔታዎች ዐይተናል።

የአድዋ ድል አውሮፓን የዓለም ፖለቲካ እና ዘር ልዕለ ኃያል ከመሆን ያስቆመ ብቸኛው አጋጣሚ ነበር። ከአድዋ በፊት ባሉ ዓመታት በርካታ የአውሮፓ እና የአሜሪካ ጋዜጦች መላው ጥቁር አፍሪካ በአውሮፓ ሙሉ ቁጥጥር ሥር የሚሆንበት ቀን መቃረቡን በእርግጠኝነት ይጽፉ ነበር። የአሜሪካኑ አትላንታ ኮንስቲቲውሽን ጋዜጣም የሚከተለውን ጽፎ ነበር።

*«መላዋ አፍሪካ በአውሮፓ መንግሥታት ቅርምት የምትጠናቀቅበት ቀን ቀርቧል» አውሮፓውያኑ በአሜሪካ ያሉትን የዘር የበላይነት በአፍሪካ ለመድገም ተዘጋጅተዋል። በአሜሪካ ቀይ ሕንዶችን በማስወገድ ለራሳቸው ዝርያ መኖሪያ መፍጠር የቻሉበትን ብቃት በአፍሪካ ለመድገምም የጥቁር አፍሪካ ዝርያዎችን በቅርቡ ማጥፋት ይጀምራሉ።»* ይሄንን የመሳሰሉ የአውሮፓ የዘር እና የፖለቲካ የበላይነት ስብከቶች በዝተው ነበር።

ይህንን የመሰለ የዘረኝነት እና የተስፋፋ የበላይነት ሕልም ነው እንግዲህ አድዋ ላይ ያከተመው። በደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ አከትሞ የጥቁር ዘር እኩልነት ከመረጋገጡ መቶ ዓመታት በፊት አድዋ ላይ ኢትዮጵያውያን የነጭ አውሮፓውያንን የበላይነት በመስበር የጥቁር እኩልነትን አረጋግጠዋል።

የአድዋን ድል ተከትሎ በመላው ዓለም ተበትነው ያሉ ትውልደ አፍሪካውያን የአድዋ፣ የምኒልክን እና የነጻይቱን አገር ኢትዮጵያን ስም በልዩ ሁኔታ ማንሣት ጀመሩ። እንደ ታላቂቷ ጽዮናዊት ኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ኃይማኖታዊ ጉዞ የሚያደርጉ ጥቁሮች ተበራከቱ። የሃይቲው ቤኒቶ ሲልቪያን እና የምዕራብ ኢንዲያው ጆሴፍ ቪታሊየን ወደ ተስፋይቱ ምድር ኢትዮጵያ ጉዞ ያደረጉ የመጀመሪያዎቹ ጥቁሮች ናቸው። እነርሱን በመከተል እንደ ቡከር ቲ. ዋሽንግተን፣ አይዳ ቢ. ዌልስ፣ ደብሊዩ ኢ.ቢ. ዱቦይስን የመሳሰሉ ታዋቂ ጥቁር አፍሪካውያን ስለ አድዋ እና





ኢትዮጵያ የነጻነት ተምሳሌትነት በስፋት ማውራት ጀመሩ። ከተወሰኑ ትውልዶች በኋላ «ብራስ ተፈሪያን» ስያሜ የሚደረገው ጉዞም የአድዋ ተፅዕኖ ውጤት ነው።

ከአድዋ በኋላ አንዳንድ የአውሮፓ አገራት እና አሜሪካ የኢትዮጵያን ድል መቀበል ሲያዳግታቸው ታይተዋል። አንዳንዶች የጣሊያንን ግዙፍነት በመጥቀስ ማንኛውንም አገር መግዛት እንደምትችል እየገለጹ የኢትዮጵያን ድል ለማኮሰስ ሞክረዋል። ነገር ግን ግዙፍ ግዛተ አፄ (ኢምፓየር) መሆን የትኛውንም አገር ከሽንፈት ሲታደገው አልታየም። በታሪክ እንደተመለከትነው እንደ ፖርቱጋል፣ ቤልጂየም እና ደች (ሆላንድ)ን የመሳሰሉ ግዙፍ ኃይሎች ሰፊ ግዛታቸው ተሸራርፏል። ጣሊያን ከእነዚህ ግዛተ-አፄዎች በምን ትለያለች?

ታሪክ በተለየ መልኩ ልዩ ክስተቶችን ይወዳል። ይህ መጽሐፍ የአድዋን ታሪካዊ ልዩ ክስተትነት ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን ለድሉ አመክንዮአዊ ማረጋገጫ ለመስጠትም የተጻፈ ነው። እንደ አድዋ ዓይነት ልዩ ክስተቶች የታሪክን ተለምዷዊ ጉዞ በማስቀየስ ሰዎች ለዘመናት ዐምነው ከተቀበሉት ንግርት የተለየ እውነታ እንዳለ ያመላክታሉ። አድዋም ለሰው ልጆች መረዳት የሰጠው ይሄንን ማረጋገጫ ነው።

አድዋ አንዲት አፍሪካዊት አገር ከወራሪ ጋር በመታገል ነፃነቷን ያወጀችበት ታሪካዊ ምስክር ነው። አድዋ ለበርካታ ቅኝ ግዛቶች በራስ የመተማመን ጉልበትን በመስጠት የዘመናት ጥርጣሬያቸውን የገለጠ ድል ነው። ከምንም በላይ ግን አድዋ የታሪክ ዑደት በተለየ አቅጣጫ የሚቀጥልበትን የጨዋታ ሕግ ያስተዋወቀ እውነታ ነው።

ፕ/ር ሬይሞንድ ጆናስ
ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ

# ክፍል አንድ

# የአድዋ መንገድ





## ምዕራፍ አንድ

## የንጉሥ ሕልም

አጋጣሚው ለዘመናዊ ፖሉቲካ ወዳጅነት ምስረታ ተስፋ ሰጪ የሆነ ዕድልን ማመልከቱ ያጠራጥራል። በዛፍ እንጨት እና በሳር ክዳን ተውቦ ከተሠራው እልፍኝ ውስጥ ወጣቱ የሸዋ ንጉሥ ባማረ ዙፋኑ ላይ እግሮቹን አደራርቦ ተቀምጧል። ራሱ ላይ ያሰረው ነጭ የሐር ሻሽ ግንባሩን በከፊል ሸፍኖት ከጀርባው በኩል ትከሻው ላይ አርፏል። እንዲህ ግርማ ሞገስ ተላብሶ የተቀመጠው ንጉሥ ምኒልክ የአንበሳ ቆዳ ለብሶ ኹለት የክብር ዘበኞች ግራና ቀኝ ታጅበ ተቀምጦ ዒሙን ያፍተለትላል።

በእልፍኙ ኹለት በሮች በኩል የሚገባው ብርሐን ከንጉሡ አጠገብ የተቀመጠውን ወጣት መሐንዲስ ያሳያል። በኤደን ከሚገኘው የስዊዘርላንድ ምህንድስና ተቋም ኢቸር ኤንድ ፉረር የተላከው ወጣት ባለ ሰፊ ደረት ሲሆን ረጅም ፂሙ ካልፍሬድ ሴኒን ወይም ፍሬድሪክ ኤንግልስ ጋር ያመሳስለዋል። ወጣቱ መሐንዲስ አልፍሬድ ኢልግ ነበር።

በ1879 ከኢልግ ጋር ሲገናኝ የምኒልክ ዕድሜ ከሠላሳ አምስት ዓመት አይበልጥም ነበር። ነገር ግን የተሸበሸበ የፊቱ ቆዳ እና የፈንጣጣ በሽታ ጥሎበት ያለፈው የጠቃጠቆ ምልክት ወጣቱን ንጉሥ ከዕድሜው በላይ ያረጀ አስመስለውት ነበር። ምኒልክ መልከ መልካም ባይሆንም በተለያየ ጊዜ ቀርበው ያነጋገሩት ሰዎች ፊቱ ላይ ስለሚነበቡት የደግነት፣ የወዳጅነት እና የአስፈሪነት ገፆች ተናግረዋል።

ፈረንሳዊው የፎቶ ግራፍ ባለሙያ አልፎንስ ኢውበሪ በ1880ዎቹ ምኒልክን አግኝቶት ነበር። ፈረንሳዊው የምኒልክን አስፈሪ ፊት ሲገልጽ አያይዞ የጠቀሰው የንጉሡን የሚያማምሩ ንቁ ዐይኖች ነበር። በተመሳሳይ ዓመት ከፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወደ ምኒልክ የተላከው ካፒቴን ሎንግ ቦይስ «የፈንጣጣ ምልክቱ

ለምኒልክ አስፈሪ ገጽታ የሰጠው ቢሆንም ከጥቋቁር ዓይኖቹ የሚወጣው የወዳጅነት አስተያየት አስፈሪነቱን በመቀነስ የንጉሡን ተወዳጅ ገጽታ ያሳያሉ›› በማለት ተናግሯል፡፡

እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ አጉስተስ ዋይልድ በበኩሉ ስለምኒልክ ባለ ስፊ ክፈፍ ጥቁር ባርኔጣ ጽፏል፡፡ የንጉሥ ባርኔጣ በዚያ ዘመን አየርላንድ ውስጥ የፀረ-ኢምፔሪያል ተቃውሞ መግለጫ መኾኑን ምኒልክ ማወቁ ቢያጠራጥርም አጋጣሚው ግን ከንጉሡ አቋም ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ጽፎ ነበር፡፡ ሌላው እንግሊዛዊ ዲፕሎማት ሰር ሬኔል ሮድ የምኒልክን ገጽታ ‹‹ኃይለኛነት የተሞላ ሲሆን ባሕርያቸው በአክብሮት የተሞላ እና ንጉሣዊ ግርማ ሞገስ የሚታይበት ነው፡፡›› በማለት ተናግሮ ነበር፡፡



*ምስል 1:* *አፄ ምኒልክ*





ከምኒልክ አጠገብ የተቀመጠው አልፍሬድ ኢልግ ባለ እንጨት ፍሬም መነፅሩ መምህር አስመስሎታል፡፡ በሰሜን ስዊዘርላንዷ ተራራማ ከተማ ፍራውንፌልድ የተወለደው ኢልግ ወደ ዙሪክ በማምራት የኹለተኛ ደረጃ ትምህርትን ተከታትሏል፡፡ በ1878 በኢቸር ኤንድ ፉረር ኩባንያ ተቀጥሮ ወደ ቀይ ባሕር አካባቢ ሲመጣ ዕድሜው ሐያ አምስት አይሞላም ነበር፡፡ ምኒልክን ለማግኘት ከሶማሌ ጠረፍ እስከ አንኮበር ያደረገው ጉዞ ፈታኝ ሆኖበት ነበር፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የሚያመሩ ተጓዥ ነጋዴዎችን ጥበቃ ዘይላ ወደብ ላይ ለሳምንታት የተጉላላ ሲሆን፤ ከነጋዴዎቹ ጋር ተገናኝቶ ጉዞ ከጀመረ በኋላም መጉላላቱ ቀጥሎ ነበር፡፡ በወቅቱ የነበሩ ነጋዴዎች ከአፋር የጎሳ አባቶች ቀረጥ ለማምለጥ ሲሉ የሚከተሉት አማራጭ መንገድ አንድ ወር ተኩል ይወስድ ነበር፡፡

አልፍሬድ ኢልግ ኢትዮጵያ እንዲመጣ የገፋፋው ከዓመታት በፊት በግብፅ ስኬታማ ቆይታ ያደረገው የአገሩ ልጅ ወርነር ሙዚንገርን ታሪክ ካነበበ በኋላ ነበር፡፡ ለግብፅ ንጉሥ ከዲቭ እስማኤል አማካሪ በመሆን በካይሮ የቆየው ሙዚንገር የንጉሡን የዘመናዊነት እንቅስቃሴ በማገዝ ይታወቃል፡፡ በ1870ዎቹ ከቀይ ባሕር እስከ ሱዳን የተዘረጋ ግዛቱን እንዲያስተዳድርለት ንጉሡ ሙዚንገርን ሾሞት ነበር፡፡ የሙዚንገርን ስኬት የተመለከተው ኢግል ለዘመናዊነት ካለው ጽኑእ ፍላጎት የተነሣ ነበር ወደ አንኮበር የዘለቀው፡፡

ወጣቱ ንጉሥ ምኒልክም ለዘመናዊነት ፍላጎት ስኬት አጋዥ እንዲሆነው ነበር ኢልግን የቀጠረው፡፡ ከምህንድስና ሙያው በተጨማሪ በቀላሉ የመላመድ ችሎታ የነበረው ኢልግ ከኢትዮጵያ አኗኗር ጋር ለመላመድ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም፡፡ ጥሙን ተላጨ፤ ኢትዮጵያዊት ሴት አግብቶ ቤተሰብ መሠረተ፤ አማርኛ ቋንቋም ተማረ፡፡ በ1884 ሠላሳ ዓመት የሞላው ኢልግ የግንባታ ዕቅድ አውጥቶ ለምኒልክ አቀረበ፡፡ ንጉሡም የቤተ መንግሥት ግንባታ ኃላፊ እና የመንገድ እና ድልድይ ሚኒስቴር አደረጉት፡፡



ምስል 1፡ አፄ ምኒልክ



*ምስል 2፦ አልፍሬድ ኢልግ፦ መጋቢት 29 ቀን 1896*

በአጭር ጊዜ ቆይታው በንጉሡ ዘንድ ታማኝነትን ያተረፈው ኢልግ በምኒልክ እና በጣይቱ ወደ አውሮፓ ተላከ። የመልዕክቱ ዋና ይዘት የነበረው ለዘመናዊት ኢትዮጵያ ግንባታ አጋዥ የኾኑ ቁሳቁሶችን መግዛት ነበር። ወደ አውሮፓ ካቀና በኋላ ንግሥት ጣይቱ ተጨማሪ ዕቃዎችን እንዲገዛላቸው ደብዳቤ ጽፈውለት ነበር። የንግሥቷ ተጨማሪ ትዕዛዝ የጫማ ቁጥራቸውን እና የተለያዩ የእርሻ ዘመናዊ ቁሳቁሶችን ዝርዝር የያዘ ነበር። ከደብዳቤያቸው ግርጌ የሚያርፈው የንግሥቲቱ ማህተም እንዲህ ይነበባል። ‹‹ንግሥት ጣይቱ፤ ብርሐን ለኢትዮጵያ››





ኢልግ ከአውሮፓ በርካታ ዘመናዊ ቁሳቁሶችን ጭኖ የመጣ ሲሆን በወቅቱ ካመጣቸው ቁሳቁሶች መካከል አንዳንዶቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ናቸው። የኅትመት መሣሪያ፣ ሰፋፊ ባርኔጣ፣ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ፣ ሳሙና፣ የተለያዩ መጫሚያዎች፣ እና ትራሶችን ጨምሮ በርካታ ቁሳቁስ ነበር ይዞ የተመለሰው።

የምኒልክን በ1889 ዘውድ መጫን ተከትሎ ኢልግ የንጉሡ አማካሪ በመሆን ተሾመ። በዘውድ አማካሪነቱም የእንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ጀርመንኛ እና አማርኛ ቋንቋ ችሎታውን በመጠቀም ጉልህ ሚናን ተጫውቷል። የከተማ ግንባታውን በመቀጠል በ1894 ከእንጦጦ እስከ ቤተ-መንግሥት የሚደርስ የውሃ መስመር ዘረጋ። ከአድዋ ጦርነት በኋላ የጣሊያን ምርኮኞችን በተመለከተ ምኒልክ የኢልግን ምክር ይጠይቁ ነበር። በአጠቃላይ ኢልግ የግንባታ ባለሙያ፣ አስተርጓሚ፣ የመሣሪያ ገዢ፣ ዲፕሎማት እና አማካሪ በመሆን ምኒልክን አገልግሏል።

የኢልግ እና የምኒልክ ወዳጅነት የተመሠረተው ለኢትዮጵያ መጥፎ ዕድል ወሳኝ በሆነ ወቅት ነበር። ወቅቱ በአሜሪካ የቅኝ ግዛት ቆይታቸው እያከተመ የነበረው አውሮፓውያን ጥቁር አፍሪካን እንደ ቀጣይ ማረፊያቸው በመመልከት አዲስ እንቅስቃሴ የጀመሩበት ነበር። በተለይም ከፈረንሳይ አብዮት እና ከናፖሊዮን ጦርነቶች በኋላ አውሮፓውያኑ አዲስ የመስፋፋት እንቅስቃሴ በመጀመር አፍሪካን የዐይናቸው ማረፊያ ያደረጉበት ነበር። በዚህም የተነሣ በደቡባዊ አፍሪካ ከ1815 በኋላ የጀመረው የአውሮፓውያን የሰፈራ ቅኝ ግዛት በሰሜን አፍሪካ ደግሞ በ1830 አልጄሪያን የመጀመሪያ መዳረሻው በማድረግ ቀጥሎ ነበር።

በ1850ዎቹ የአትላንቲክ የባሪያ ንግድ እያከተመ የነበረ ቢሆንም የቤልጂየሙ ንጉሥ እንደ አዲስ የጀመረው የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴ የአህጉሪቷን የማይነጥፍ የባሪያ አቅርቦት ለተቀሩት አውሮፓውያን ጠቁሟል። እንደ ፖርቱጋል፣ ሆላንድ እና ቤልጂየምን የመሳሰሉ ትናንሽ ሐገራት በአፍሪካ ታላቅ ሕልማቸውን ማሳካት እንደሚችሉ ያሳዩበት ወቅትም ነበር።



ክትናንሽ የአውሮፓ አገራት እንቅስቃሴ ጎን ለጎን ትላልቆቹ አገራት አብዛኛውን የአፍሪካ ክፍል በስፋት መያዝ ጀምረው ነበር። ታላቋ ብሪታኒያ ከካይሮ እስከ ደቡባዊው የአፍሪካ ጫፍ ለመያዝ ስትንቀሳቀስ፣ ፈረንሳይ በበኩሏ ሰሜን እና ምዕራብ አፍሪካን ዋና መቀመጫ በማድረግ በምሥራቅ አፍሪካ የሶማሊያ ጠረፍ አካባቢ ተጨማሪ ይዞታን አስከብራለች። የጀርመኑ መራሄ መንግሥት ቢስማርክ በ1884 አውሮፓውያኑን በርሊን ላይ በመሰብሰብ የአፍሪካ ቀጣይ ዕድል በአውሮፓውያን ብቻ እንደሚወሰን አስረግጦ በመናገር ቅርምቱ ሰላማዊ የሚሆንበትን መንገድ አመቻቸ። እንግዲህ አልፍሬድ ኢልግ እና ምኒልክ በ1878 ሲገናኙ የአፍሪካ ዕጣ ፈንታ በአውሮፓውያን እጅ ላይ ሲወድቅ ተቃርቦ ነበር።

## በቴዎድሮስ ላይ የተደረገው ዘመቻ፡- የወረራ ቅድመ ሁኔታ

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ በበርካታ ግዛቶች ተከፋፍላ ተጠሪነታቸው ለይስሙላ ለተቀመጡ ንጉሠ-ነገሥት ባደረጉ በርካታ ነገሥታት ትተዳደር ነበር። ከምኒልክ በፊት በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ኹለት ጠንካራ ንጉሠ-ነገሥታት ቴዎድሮስ እና ዮሐንስ ነበሩ። ኹለቱም ነገሥታት ከግዛት አስተዳዳሪነት ተነሥተው ዘውድ ለመጫን የበቁት ሽፍትነትን እንደ አማራጭ በመጠቀም ነበር። በኢትዮጵያ ቀደምት ፖለቲካ ባሕል መሠረት ሽፍትነት ሥልጣን ለማግኘት ዓይነተኛ መንገድ እንደሆነ ይታመናል።

የቴዎድሮስ የንግሥና ጉዞ የጀመረው በሽፍትነት ነበር። በ1818 ምዕራብ ጐንደር አካባቢ የተወለደው ካሳ ሃይሉ አባቱ በልጅነቱ ጥሎት ስለሸፈተ በእናት ብቻ ለማደግ ተገድዶ ነበር። በወጣትነት ዘመኑ የነበሩ ፖለቲካዊ ተቀናቃኞቹ ከዝቅተኛው ማሕበረሰብ መገኘቱን ደጋግመው በማንሳት ያሸሟጥጡት ነበር። በተለይም የእናቱን ኮሶ ሻጭነት በማንሳት ስለ መሠረተ-ድህነቱ እና ዘረ-ቢሥነቱ የሚናገሩ በርካቶች ነበሩ።

በወጣትነት ዕድሜው ነበር ካሳ ኃይሉ ሽፍትነትን እንደ ፖለቲካዊ ተቃውሞ መግለጫ በመጠቀም የሥልጣን ጉዞውን የጀመረው። በመቀጠል በግዛቱ ባገኘው ተቀባይነት እና በፈጸመው ፖለቲካዊ ጋብቻ በመንጠላጠል የዘውድ ተቀናቃኞቹን





አንድ በአንድ አስወገደ። በ1855 አፄ ቴዎድሮስ በሚለው የንግሥና ስሙ በደረስጌ ማርያም ቤተክርስቲያን ዘውድ ሲጭን የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት በማረጋገጥ «ክርስቲያናዊት ኢትዮጵያን» በቀጠናው ልዕለ-ኃያል የማድረግ ዓላማን አንግቦ ነበር። ለዓላማው መሳካት ቁልፍ እገዛ ያደረገለት የ33 ዓመቱ እንግሊዛዊ አማካሪው ዋልተር ፕላውደን ወደ ለንደን በርካታ ደብዳቤዎችን በመጻፍ ስለ አፄ ቴዎድሮስ የዘመናዊነት ሕልም ለንግሥቲቷ አሳውቋል።

ዋልተር ፕላውደን ለእንግሊዟ ንግሥት በተደጋጋሚ በጻፉቸው ደብዳቤዎቹ አፄ ቴዎድሮስ የባሪያ ንግድ ማስቀረታቸውን ጠቅሶ አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነቷን እንድታጠናክር መክሯል። ክርስትናን እንደ ኹለትዮሽ ግንኙነት መሠረት በመጥቀስም እንግሊዝና እና ኢትዮጵያ እስላማዊውን የግብጽ መንግሥት በጋራ መቋቋም እንደሚችሉም ፕላውድን ለንግሥቷ አስተያየት ሰጥቶ ነበር።

አፄ ቴዎድሮስ ዘውድ በጫኑ ማግስት ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ ደጋማ ግዛቶች ጀምሮ እስከ ቀይ ባሕር ዳርቻ የሚደርስ ክርስቲያናዊ ግዛተ-አፄ የመገንባት እንቅስቃሴያቸውን ጀመሩ። በ1856 ወደ ሸዋ በመዝመት ግዛቱን ሙሉ በሙሉ አስገበሩ። ቴዎድሮስ ሸዋን ባስገበሩ ማግስት የሸዋው ንጉሥ ሳህለ-ሥላሴ በሕመም ምክንያት ዐረፉ። አፄ ቴዎድሮስም የንጉሡን ልጅ ምኒልክን ወደ ጐንደር ይዘው ተመለሱ። ምኒልክም ከጎንደር አምልጦ ወደ ሸዋ እስከተመለሰበት ወቅት ድረስ በግዞት በአፄ ቴዎድሮስ ሥር ቆይቷል። ከሸዋ በመቀጠል ወደ ሙስሊም ኦሮሞዎች ግዛት እና የቀይ ባሕር ዳርቻ የሙስሊም ከተሞች ያደረጉት ዘመቻ ለአፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት ቀላል ድል አላስገኙላቸውም ነበር።

ከንግሥናም በኋላ የቀጠለው የአፄ ቴዎድሮስ ሽፍታዊ አስተዳደር እና ዘመቻ ለንጉሡ ያተረፈላቸው ነገር ቢኖር በአገር ውስጥ ዐመኔታን ማጣት ነበር። በየዘመቻው ወቅት ወታደሮቻቸው የሚያሳዩት ሽፍታዊ ባሕርይ ገበሬውን አማረረው። በተለይም ምርቱን እና ከብቱን በአፄ ቴዎድሮስ ወታደሮች እየተቀማ የተቸገረው ገበሬ

ለንጉሡ ከስ ሲያሰማ የተሰጠው ምላሽ «ገበሬው ወታደሩን የመመገብ ግዴታ አለበት» የሚል ነበር። በዚህ የተነሣም ገበሬው ለአፄ ቴዎድሮስ «አባ በዝብዝ» የሚል ቅፅል ስም ሰጣቸው። በመቀጠልም ገበሬዎች ምርት እና ከብቶቻቸውን መሸሸግ ጀመሩ። አፄ ቴዎድሮስም መደናገጥ የጀመሩት በዚያ ወቅት ነበር።

ከአገር ውስጡ ችግር በተጨማሪ የአውሮፓውያኑ የዘገየ ምላሽ እና ዝምታ ንጉሡን አበሳጫቸው። በ1862 ለንግሥት ቪክቶሪያ የፃፉት ደብዳቤ በእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ታፍኖ በመቅረቱ መልስ አልተላከላቸውም ነበር። በዚህ የተበሳጩት አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን የእንግሊዝ ሚሲዮናውያን ጠራርገው በማሠር ለክርስቲያናዊት ኢትዮጵያ ወንጌል ሰባኪ እንደማያስፈልጋት ተናገሩ። እሥረኞቹን በማስገደድም በመንገድ ግንባታ እና የተለያዩ ሥራዎች አሠማሩ። ንጉሡ «ሴባስቶፖል» የሚል ክርስቲያናዊ ስም የሰጡትን መድፍም ያሰሩት በዚያ ወቅት ነበር።

ከሚሲዮናውያኑ በመቀጠል የእንግሊዝ ቋሚ መልዕክተኞችን አሠሩ። እሥረኞቹን እንዲፈቱ በእንግሊዝ መንግሥት በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ንጉሡ በእምቢታቸው ጸኑ። ይባስ ብለውም በ1867 እስረኞችን እንደማይፈቱ በግልጽ አሳወቁ። በቀጣዩ ዓመት እንግሊዝ የታገቱ ዜጎቿን ለማስፈታት በጀነራል ሮበርት ናፒየር የተመራ ጦሯን ወደ ኢትዮጵያ አዘመተች።

በወርኃ ጥር 1868 የእንግሊዝ መርከቦች ከምጽዋ በስተደቡብ የምትገኘው ዙላ ወደብ ደረሱ። በሺዎች የሚቆጠሩ የሕንድ ቅጥረኞች፣ የእንግሊዝ ወታደሮች እና ወደ ኹለት ሺህ የሚጠጉ የቻይና መንገድ ሠራተኞችን ጨምሮ አጠቃላይ ከሐያ ሺህ በላይ ሠራዊት ዙላ ላይ ተራገፈ። ከወታደሮቹ በተጨማሪ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የጋማ ከብቶች እና አርባ አምስት የሕንድ ዝሆኖች ይገኙበት ነበር። የናፒየር ዘመቻ አወቃቀር በወቅቱ የእንግሊዝን ኹለንተናዊ ኃይል ለማሳየት በይሁንታ የታቀደ ነበር።







... Napier Expedition. From Roger Acton. The Abyssinian Expedition and the Life and ... London: Illustrated London News, 1868.

ምስል 3፡ የናፒየር ዘመቻ- ከሮጀር አክተን ምስል ላይ የተወሰደ (ለንደን ኒውስ፤ 1868)

በሳምንታት በኋላ የናፒየር ጦር ከቀይ ባሕር ዳርቻ ወደ ተራራማው ማዕከላዊ የኢትዮጵያ ግዛት የሚያደርገውን ጉዞ አጋመሰ። በሕንዳውያን ቅጥር ወታደሮች የሚነዱት ዝሆኖች ያልተገጣጠሙ አርምስትሮንግ የጦር መሣሪያዎች ተሸክመው ነበር።

ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት አፄ ቴዎድሮስ በጉዞ ላይ የነበረው የናፒየር ጦር ላይ የሽምቅ ውጊያ ቢከፍቱ ኖሮ ውጤቱ የተለየ ይሆን ነበር። ነገር ግን አፄ ቴዎድሮስ የመረጡት አካሄድ ወታደሮቻቸውን ጥቂት ዘመናዊ ጠመንጃ፣ ጦር እና ጎራዴ አስታጥቀው በስቅለት ዕለት ሚያዝያ 10 ከመድፈኛ እና እልም ተኳሽ የናፒየር ወታደሮች ጋር መግጠምን ነበር።



he Napier expedition. From Roger Acton, *The Abyssinian Expedition and the Life and eign of King Theodore*. London: Illustrated London News, 1868.

የናፒየር ዘመቻ- ከሮጀር አክተን ምስል ላይ የተወሰደ (ለንደን ኒውስ፤ 1868)

ውጤቱን ማንም ሊገምተው የሚችል ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሲሞቱ ከሐያ ያልበለጡ የናፒየር ወታደሮች ቆሰሉ። አፄ ቴዎድሮስ ለድርድር ጥያቄ ከማቅረብ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። የተወሰኑ እሥረኞችን ከለቀቁ በኋላ አንድ ሺህ የቀንድ ከብት እና አምስት መቶ በጎችን ለናፒዬር ወዳጅነት ስጦታ በማቅረብ የድርድር ጥያቄ አቀረቡ። ነገር ግን ናፒየር ጥያቄውን ባለመቀበል ግስጋሴውን ቀጠለ።

የናፒየር ወታደሮች መቅደላ ላይ ወደሚገኘው የንጉሡ የመጨረሻ ምሽግ ሲቃረቡ የቴዎድሮስ ጦር በአንፃሩ መበታተን ጀምሮ ነበር። የእንግሊዝ ሠራዊት ወደ ተራራው በመውጣት እሥረኞቻቸውን ለማስፈታት እንቅስቃሴ ጀመሩ። በዚያ ቅፅበት ነበር አፄ ቴዎድሮስ በሽጉጣቸው እራሳቸውን ያጠፉት።

እንግሊዝ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝም ሆነ የተለየ ዓላማ አልነበራትም። የእንግሊዝ ፀብ ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር እንጂ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አልነበረም። ዘመቻው እንደተጠናቀቀ ናፒየር ጓዙን ሸክፎ የመልስ ጉዞ የጀመረውም ለዚህ ነበር።

የእንግሊዝ ጦር ከኢትዮጵያ ሲወጣ ለቀጣይ ወረራ የሚሆን መንገድ አመቻችቶ ነበር። ለናፒየር ጦር መተላለፊያ በማመቻቸትና መንገድ በመምራት ልዩ እገዛ ላደረገው ለትግራዩ ካሳ በርካታ የጦር መሣሪያዎችን በመስጠት ነበር ናፒየር ውለታውን የመለሰው። የአፄ ቴዎድሮስ መወገድ እና በእጁ የገባው የእንግሊዝ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የትግራዩ ካሳ በቀጣይ ለሚያደርገው የዘውድ ግስጋሴ ቀና መንገድ እንደሚፈጥሩለት ግልጽ ነበር።

እንግሊዝ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝ ፍላጎት ባይኖራትም የናፒየር ዘመቻ ግን ፍላጎቱ ለነበራቸው ግብፅ እና ጣሊያን እንደ መነሻ ማገልገሉ አልቀረም። እንግሊዞቹ ከአገር ውስጥ የኃይል ተፎካካሪ ጋር በማበር እንዴት ንጉሠ ነገሥት





ማስወገድ እንደሚቻል ለግብጽ እና ለጣሊያን አሳይተዋል። ናፒየር የትግራዩን ካሳ በቴዎድሮስ ላይ በማሥነሳት የተሳካ ዘመቻ ማድረጉ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሠራዊት ደካማ የውጊያ ብቃት ለማሳየት ችሏል።

## የግብፅ በኢትዮጵያ ላይ መነሳት

ከአፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ባሉት ሦስት ዓመታት የትግራዩ ካሳ ከእንግሊዝ ባገኘው የጦር መሣሪያ በመታገዝ ተቀናቃኞቹን በማስወገድ ሥልጣኑን በእጁ ለማማከል ተንቀሳቀሰ። በወርኃ ጥር በ1872 በአክሱም ጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን «አፄ ዮሐንስ አራተኛ» በሚል የንግሥና ስም ዘውድ ጫኑ።

የናፒየርን ዘመቻ ተከትሎ በኢትዮጵያ የተፈጠረውን አለመረጋጋት በመጠቀም ግብፅ የመስፋፋት እርምጃዋን ጀመረች። ኮዲቭ እስማኤል የግብፅን ጥንታዊ ክብር ለመመለስ በማሰብ የግዛት ማስፋፋት እንቅስቃሴውን ወደ ሱዳን፣ ኢትዮጵያ እና ሱማሌ ማድረግ ጀመረ። በ1865 ምፅዋን በመቆጣጠር ስዊዘርላንዳዊውን ወርነር ሙዚንገር የግዛቱ አስተዳዳሪ በማድረግ ምፅዋ ላይ አስቀመጠው።

ከናፒየር ተሞክሮ በመነሳት ኮዲቭ እስማኤል ከኢትዮጵያ ውስጥ በመሆን አፄ ዮሐንስን የሚያዳክምለት ወዳጅ ማፈላለግ ጀመረ። የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ የግዛት ነጻነት እንደሚፈልግና የዮሐንስን ንጉሠ ነገሥትነት ላለመቀበል እንደሚያንገራግር ሲሰማ እስማኤል አጋጣሚውን ሊጠቀምበት ወሰነ። ምኒልክ ከጀርባ አፄ ዮሐንስን እንደሚያዳክምለትም ተስፋ አደረገ።

በ1875 ግብፅ ሐረርን በመቆጣጠር ከሸዋ ወደ ጅቡቲ የተዘረጋውን የምኒልክ የንግድ መሥመር ዘጋች። የምኒልክን ወጪ እና ገቢ ንግድ በማስተጓጎል ዓላማዋን ለማሳካትም ተስፋ አደረገች። እንደ ተጨማሪ መደለያ ለምኒልክ ዘመናዊ የጦር

መሣሪያ በማቅረብ ከአፄ ዮሐንስ ጋር ለሚያደርገው ፉክክር እገዛ ለማድረግ ቃል ገባች።

በሰሜን የአገሪቱ ክፍል ጠንካራ ድጋፍ የነበረው አፄ ዮሐንስ ለግብፅ ተደጋጋሚ ትንኮሳ የሚሸበር አልሆነም። በተለይም የንጉሡ አስተዳደራዊ ፍጹምነትና በክርስትና ዕምነት ላይ የተመሠረተ መኾኑ የግብፅን እስላማዊ ኃይል ለመመከት ሕዝቡን በቀላሉ ማስተባበር ችሎ ነበር። ይሄንን በመመልከት ግብፅ የሙስሊም ሕዝቦች መኖሪያ የኾኑትን የቀይ ባሕር ዳርቻ፣ ምፅዋ እና የሐረር አካባቢን ተቆጣጠረች ያዘች።

በ1875 ግብፅ ቁጥሩ ወደ ዐሥራ አምስት ሺህ የሚጠጋ ጦሯን በዮሐንስ ላይ አዘመተች። የግብፅን ጦር ይመሩ የነበሩት በ1860ዎቹ በአውሮፓ የተለያዩ የጦር ሜዳዎች ላይ የተሰለፉ የዴንማርክ፣ ጀርመን እና የኦስትሪያ ወታደራዊ መኮንኖች እና ከአሜሪካ የሲቪል ጦርነት የተረፉ የጦር መኰንኖች ነበሩ። የዘመቻው ዋና ዓላማ አፄ ዮሐንስን በማስወገድ ከቀይ ባሕር በስተምዕራብ እና ከመረብ ወንዝ በስተሰሜን የሚገኘውን ግዛት በቁጥጥር ሥር ማዋል ነበር።

በዘመቻው ዕቅድ መሠረት የምፅዋው ገዥ ሙዚንገር ለምኒልክ የጦር መሣሪያ ለማድረስ ተንቀሳቀሰ። ነገር ግን ቁጥሩ ወደ አራት መቶ የሚጠጋው የሙዚንገር ኃይል ምኒልክ ጋር አልደረሰም። በሕዳር 7 ቀን 1875 በሸዋ የንግድ መስመር ላይ ሕልውናቸው የተመሠረተው የአፋር ሕዝቦች የሙዚንገርን ሠራዊት፣ ኢትዮጵያዊት ሚስቱን እና ልጁን ጨምሮ ገደሏቸው። በተመሳሳይ ሰሌት በሰሜን ግንባር የተንቀሳቀሰው የግብፅ ጦር ጉንደት ላይ በዮሐንስ ሠራዊት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት ተፈታ።

ከጥቂት ወራት በኋላ በአሉላ የተመራ የዮሐንስ ልዩ ኃይል የግብፅን ጦር ጉራ ላይ ድል በመንሳት ከግማሽ በላይ የሚኾኑትን የግብፅ ሠራዊት ሙት እና ቁስለኛ አደረገ። ከጉራው ሽንፈት በኋላ የእስማኤል የተስፋፊነት ሕልም ሙሉ በሙሉ





ጨለመ። ከሦስት ዓመት በኋላ ለእስማኤል መንግሥት መወገድም የጉራ ሽንፈት አስተዋፅዖ ነበረው። ከደማቁ የጉራ ድል በኋላ ኢትዮጵያ ግዛቷን በማስከበር ኤርትራን ጠቅልላ ፖለቲካዊ ድንበሯን የቀይ ባሕር ዳርቻ አደረገች።

በጉራ ላስመዘገበው ደማቅ ድሉ አፄ ዮሐንስ ለጦር መሪያቸው አሉላ የራሥነት ማዕረግ ሰጡት። በመቀጠልም መቀመጫውን አስመራ በማድረግ ባሕረ ነጋሽን እንዲያስተዳድር ሾሙት። ሰሜናዊውን ቀጠና ለራስ አሉላ በመስጠት አፄ ዮሐንስ ትኩረታቸውን ወደ መሃል አገር አደረጉ።

አፄ ዮሐንስን በግብፅ ወራሪ ኃይል ተፅዕኖ ሥር የወደቁ ሙስሊም ሕዝቦችን በ1880 በመሰብሰብ የክርስትና ዕምነት እንዲቀበሉ፣ አለበለዚያ አገሪቷን ለቀው እንዲወጡ አዘዙ። በመቀጠል ከምኒልክ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር በ1882 ወንድ ልጃቸው ለምኒልክ ሴት ልጅ ዳሩ። ከፖለቲካዊ ጋብቻው በተቃራኒ ምኒልክ የዮሐንስን ዘውድ ለመንጠቅ የተለየ መንገድ ለመጠቀም ወሰኑ። በዚህም ከአፄ ዮሐንስ ጋር የገቡበትን ፖለቲካዊ ጋብቻ በመሠረዝ በጣይቱ ፖለቲካዊ ድጋፍ እየታገዙ ሥልጣኑን የሚቀሙበትን ወቅት መጠባበቅ ጀመሩ።

## የኢትዮጵያ የምንጊዜም ኃይለኛ ጥንዶች፦ ምኒልክ እና ጣይቱ

ጣይቱ ብጡል ክብረት የጠነከረ ልብ ያላቸው ሴት ነበሩ። ምኒልክ ከጣይቱ ጋር ጋብቻ ሲፈጽሙ የሸዋ ንጉሥ ብቻ የነበሩ ቢሆንም ኢትዮጵያን የመምራት ጽኑእ ፍላጎት ነበራቸው። እንደ ቀደምቶቻቸው ቴዎድሮስ እና ዮሐንስ ኹሉ የምኒልክም የዘር ሐረጋቸው ከንጉሥ ሰለሞን እና ንግሥተ ሳባ እንደሆነ ይታመን ነበር። የኹለቱ ጋብቻ ለጣይቱ ብጡል የንግሥና ትንቢት ፍፃሜን አስገኝቶላቸዋል።




Empress Taytu. From *Le Petit Journal*, 29 March 1896.

ምስል 4፦ ጣይቱ ብጡል፣ ከሌ ፒቲ ጋዜጣ የተወሰደ (መጋቢት 29 ቀን 1896)





ጣይቱ ብጡል በመልክ መልካምነታቸው እና በሩኅሩኅነታቸው ይታወቃሉ። «የአረብ» ዝርያ ካላቸው ኦሮሞ አያቶታቸው እንደወረሷቸው የሚገመተው ረጃጅም ጣቶቻቸው እና ነጣ ያለ የቆዳ ቀለማቸው ለንግሥቷ ተጨማሪ ውበት ሆኗቸዋል። ሰፊ የእርሻ መሬት እና በርካታ የቤት እንስሳት ባለቤት የኾኑት ጣይቱ ብጡል ከምኒልክ ጋር ከመጋባታቸው በፊት አስቀድሞ ባለጸጋ ነበሩ።

የምኒልክ እና ጣይቱ ጋብቻ በዘመናዊ ፖለቲካ ውስጥ ወደር የማይገኝለት ጋብቻ ነበር። ኹለቱ ጥንዶች በፍጹማዊ መከባበር እና ልባዊ ፍቅር አብረው ኖረዋል። ከመጋባታቸው በፊት ኹለቱም በየፊናቸው ትዳር ነበራቸው። ወጣቱ ምኒልክ ከልዕልት አልጣሽ ቴዎድሮስ ጋር ያደረገው ጋብቻው የመጀመሪያው የነበረ ሲሆን ጋብቻው ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ አልዘለቀም ነበር። ቀጥሎ ባፈና ከተባለች መልከመልካም ሴት ወይዘሮ ጋር ጋብቻ ፈጸሙ። እስከ ጣይቱ መምጣት ድረስ ምኒልክ በመልከኛዋ ባፈና ተፅዕኖ ሥር ነበሩ። በ1883 የፋሲካ ዕለት ከጣይቱ ብጡል ጋር ያደረጉት ጋብቻ ከቀድሞዎቹ ኹለት ጋብቻቸው በተለየ መልኩ የተጠና ነበር።

የምኒልክ እና ጣይቱ ጋብቻ በኹሉም ረገድ እንከን አልባ ነበር። ምኒልክ የንጉሥ ሕልም የነበረው ታላቅ ባል ሲሆን፤ ጣይቱ ደግሞ ሐብት፣ ፖለቲካዊ ብስለት እና ከሰሜኑ የአገሪቷ ክፍል ጋር ጥብቅ ቁርኝት ነበራት። የኢትዮጵያ ቀደምት ነገሥታት ከሰሜን አካባቢ የተነሡ በመሆናቸው ለምኒልክ የዘውድ ጉዞ የሰሜኑ ሕዝብ ይሁንታ ወሳኝ ነበር። ጣይቱም ለምኒልክ ይዘውለት የመጡት ይሄንኑ ወሳኝ የመጫወቻ ካርድ ነበር። በሰሜን አካባቢ የተወለዱት ጣይቱ ብጡል ቤተሰቦቻቸው በጌምድር እና ትግራይን ጨምሮ በሰሜን ሰፊ ዕውቅና ነበራቸው። ከሸዋ የአገሪቷ ክፍል ለመጡት ምኒልክ የሰሜኑን ሕዝብ ተቀባይነት ያስገኙላቸው ጣይቱ ብጡል ነበሩ።

በፖለቲካው ረገድ የጣይቱ አንደበተ ርቱዕ መሆን እና ያላቸው ተሰሚነት ለምኒልክ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል። ጣይቱ ብጡል ከሙስሊም ኦሮሞ ቤተሰብ



S. M. TAÏTOU
Impératrice d'Abyssinie

Empress Taytu. From *Le Petit Journal*, 29 March 1896.

ምስል 4፡- ጣይቱ ብጡል፣ ከሌ ፔቲ ጋዜጣ የተወሰደ (መጋቢት 29 ቀን 1896)

እንደተወለዱ እና ቤተሰቦቻቸው ከዐሥራ ስምንተኛው ክፍለዘመን ጀምሮ የክርስትናን ዕምነት እንደተቀበሉ ይነገራል። ከዚያ ጀምሮ የጣይቱ ቤተሰቦች መቀመጫቸውን በሰሜን በማድረግ ከፍተኛ ሀብት እና ተቀባይነት አፍርተዋል። የሚስታቸው ተቀባይነት ነበር ለምኒልክ የሥልጣን ጉዞ መንገዱን ያቀለለላቸው።

ንግሥት ጣይቱ በጠንካራ ፖለቲካዊ አቋማቸው ይታወቃሉ። በተለይ ለአውሮፓውያን የነበራቸው ጥርጣሬ እና የማይወላውል አቋም ከምኒልክ በላይ አስፈሪ አድርጓቸው ነበር። በቤተ-መንግሥት ውስጥ ፀረ-አውሮፓዊ አቋም የነበራቸውን ኀዘዛዦች በማስተባበር በተደጋጋሚ የምኒልክን ውሳኔ ማስቀልበስ ችለዋል። የምኒልክ ፖለቲካዊ ማዕከል በአዲስ አበባ እንዲሆን ካስደረጉ በኋላ ንግሥቲቷ የመዲናዋ ዋና ፖለቲካዊ ተዋናይ በመሆን ቀጠሉ።

ምኒልክ ለትዳራቸው ታማኝ እንዳልነበሩ ይነገራል። የንጉሡን በርካታ ቅምጦች በመታገስ ጣይቱ በሆደ ሰፊነት ኑሮአቸውን ገፍተዋል። ከየትኛዋም የንጉሡ ቅምጦች ጋር እሰጥ አገባ ውስጥ ገብተው አያውቁም ነበር። በአንድ ወቅት አንዷን የምኒልክ ቅምጥ በመርዝ መግደላቸው ተወርቶ ነበር። ንግሥቲ ትዳራቸውን ለማስከበር የተለየ እንቅስቃሴ አለማድረጋቸውን የተመለከቱ አንዳንድ ሰዎች ‹‹የዛሬዋ ንግሥት ነገ ተራ ሴት ወይዘሮ ልትሆን ትችላለች›› በማለት ተናግረው ነበር።

የንግሥት ጣይቱ ዕለታዊ እንቅስቃሴ የተጠና እና ዕይታ ለመሳብ ተብሎ የሚደረግ ነበር። ንግሥቲቷ አሻቢ ወይዛዝርቶችን ሲመርጡ የአሻቢዎቻቸው ቆዳ ጠቆር ያለ እንዲሆን ያመቻቹና የራሳቸው ወርቃማ የቆዳ ቀለም ጎልቶ እንዲታይ ያደርጉ ነበር። በመሃል አዲስ አበባ ሰጋር ፈረሳቸው ላይ ሆነው ሲዘዋወሩም የወርቅ ዘርፍ ያለው ጃንጥላ ይይዙ ነበር። እንቅስቃሴያቸው ፖለቲካዊ ዕውቅናቸውን ቢያጎላውም በተደጋጋሚ ለዕይታ መውጣታቸውን አንዳንድ ወግ አጥባቂ ኃይማኖተኞች አልወደዱላቸውም ነበር።





የበርካቶችን ተቃውሞ ንቀው በመተው ጣይቱ የአደባባይ እንቅስቃሴያቸውን ቀጠሉበት። ቀስ በቀስም ፖለቲካዊ ሥልጣናቸውን ማሳየት ሲጀምሩ በተቃዋሚዎቻቸው ዘንድ ሳይቀር ከበሬታን አገኙ። ጣይቱ ስለሚጠሏቸውም ሆነ ስለሚቃወሟቸው ሰዎች ግድ አልነበራቸውም። በመጨረሻም ፖለቲካዊ ሥልጣንን እንደ ማኪያቬሊ መረዳት የጀመሩት ጣይቱ ብጡል የሚፈልጉትን አገኙ። ይኸውም ደጉ ባለቤታቸው ምኒልክ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ ሲሆን ጣይቱ ደግሞ ተፈሪ ኾኑ።

# ምዕራፍ ኹለት

## ጉዞ ወደ አድዋ

በኔፕልስ የሚገኙ መጠጥ ቤቶች ከአፍ እስከ ገደፋቸው ሞልተዋል። ከተለያዩ የጣሊያን ወታደራዊ ሰፈሮች የመጡት የጦር ሠራዊት አባላት በኔፕልስ የሚያደርጉትን የመጨረሻ የጥቂት ሰዓታት ቆይታ ለመሰናበት ራሳቸው በመጠጥ እያዝናኑ ነበር።

የጣሊያን የወደብ ከተማ የሆነችው ኔፕልስ ወታደሮች ለጉዞ በሚዘጋጁበት ወቅት የተለየ ድባብ ትላበሳለች። ወደ ግራኒሊ የጦር ሰፈር ወታደሮችን ይዞ የሚያልፈው ባቡር ኔፕልስ ላይ ቆሟል። ተሳፋሪ ወታደሮችም ከባቡሩ በመውረድ በወደቧ ያሉትን መጠጥ ቤቶች እና ካፍቴሪያዎች ሞሉ። በጂያርዲኖ ዲ ኢታሊያ የሚገኘው መጠጥ ቤት ለደንበኞቹ የምሽቱን የመጨረሻ ዙር መጠጥ ቀዳላቸው።

በማግስቱ ጠዋት ግራኒሊ የሚገኙት ወታደሮች ለጉዞ ዝግጅታቸውን እያከናወኑ ነበር። ከመስታወት ፊት ቆሞ የደረት ኒሻኑን የሚያስተካክለው ጄራርዶ ፓንታኖ በኩራት የራሱን ምስል ተመለከተ። የፊቱ ገጽ ላይ ፍጹም ሰላማዊ መረጋጋት ቢመለከትም ስለ ወደፊቱ እርግጠኝነት አልተሰማውም። በተለይም ስለሚሄድበት የአፍሪካ አሕጉር ያለው ዕውቀት ውሱን መሆን አስፈርቶት ነበር።

ነጭ ሸሚዝና ሱሪ እንዲሁም ቦቲ ጫማ ያደረጉ ወታደሮች በመርከቡ መወጣጫ ወደላይ እየጎረፉ ነበር። ደረቅ መሬት ላይ የተሰበሰቡት ሲቪል ዜጎች ለተጓዥ ዘመዶቻቸው ነጭ መሃረቦቻቸውን በማውለብለብ የመጨረሻውን ስንበት በማድረግ ላይ ናቸው። ሌተናንት ፓንታኖ በወታደራዊው ልብስ ያሸበረቁ ወታደሮች ወደ መርከቧ ሲገቡ ተመለከተ።





የመርከቧ ልዩ ክፍል ውስጥ ፓንታኖ እና የልጅነት ጓደኛው ኡምቤርቶ በዝምታ ተቀምጠዋል። ኹለቱም ወደ አፍሪካ ሲዘምቱ የመጀመሪያቸው ነበር። ቀድሞ አፍሪካን የሚያውቁ የጉዞ አጋሮቻቸው የሚያወሩትን በጥሞና ነበር የሚያዳምጡት። ከኹለቱ ጋር በመጓዝ ላይ ከነበሩት መካከል በአቆርዳት ደርቡሽ ላይ ላስመዘገበው ድል ሜዳሊያ የተሸለመው ሌተናንት ቦራ፣ አረብኛ አቀላጥፎ የሚናገረው መድፍ ተኳሹ ሌተናል ካሩሶ እንዲሁም ስለ አፍሪካ በሰፊው የሚዘግበው የትሪቡና ጋዜታ ዘጋቢ ሉጂ መርካቴሊ ይገኙበታል።

ፓታኖን እና ወታደሮቹን ያሳፈረችው የመንገደኞች መርከብ «ፖ» የሚል ስያሜ ነበራት። ጣሊያን ጦር ሠራዊቷን ወደ ውጭ አገር ስትልክ እንደ ፖ ያሉትን የመንገደኞች መርከብ የመጠቀም ልማድ አላት። ፓታኖ መርከቧ ላይ የወጣው በመስከረም አጋማሽ 1894 ዓ.ም ነበር። ከወታደሮቹ ጋር አብረው የሚጓዙ በርካታ ሲቪሎች ተሳፍረዋል። ከተሳፋሪዎቹ መካከል በወቅቱ በመላው አውሮፓ ዝናቸው በመናኘት ላይ የነበሩት «ጉይላሜ እህትማማቾች» የሰርከስ ቡድን ይገኝበታል። የሰርከስ ቡድኑ ከወታደሮቹ ጋር የሚጓዘው እስከ እሌክሳንድሪያ ብቻ ነበር። በአሌክሳንድሪያ ትርኢታቸውን ካሳዩ በኋላ ደግሞ ዕድል ወደሚጠራቸው ቦታ ያመሩና በመጨረሻም ወደ አውሮፓ ይመለሳሉ።

ባለ ሦስት ምሰሶዋ የእንፋሎት ሞተር መርከብ ፖ የተለያዩ የመንገደኞች ቁሳቁሶችን ከጫነች በኋላ ለጉዞ ዝግጁ ሆነች። ፓታኖ እና ፐርቲኒ የመርከቧ የላይኛው ወለል ላይ ሆነው የወደቡን እይታ በመሰናበት ላይ ነበሩ። ከኹለቱ መኮንኖች ጋር የጉይላሜ እህትማማቾች ወለሉ ላይ ነበሩ። ለትርኢት የሚያቀርቧቸው ዝንጀሮ፣ አዕዋፍ፣ ድብ እና የመሳሰሉት እንስሳትም በፍርግርግ ውስጥ ተቆልፎባቸው የተጫኑት በዚሁ የመርከቧ የላይኛው ወለል ላይ ነበር።

ጣሊያን ከሚገኘው ግዙፍ ወንዝ ስያሜዋን ያገኘችው ፖ የኔፕልስን ወደብ ወደ ኋላ በመተው ጉዞዋን ጀመረች። ጥንታዊ ወደቦች በሆኑት ሶሬንቶ እና ካፕሪ

መካከል አድርጋ የምትሯሯጥ ጭስ እያሳየች ጉዞዋን ቀጠለች። የዓሣ አጥማጆች መኖሪያ የኾኑትን ፕሮሲዳ እና ኢስቺያንም አለፈቻቸው።

የኔፕልስ ወደብ ከዕይታው ሲሰወር መኮንኑ ፓታኖ የመርከቧን ግድግዳ መመልከት ጀመረ። ፖ በእርግጥም ያረጀች መርከብ ናት። የተሰነጣጠቀ እና የዛገ ግድግዳዋን በወርቅማ ቀለም ለመሸሸግ ተሞክሯል። መርከቧ ደቡባዊ አቅጣጫን በመያዝ የሜሲናን ሰርጥ አልፋ ወደ ዋናው የውኃ አካል ገባች። ፓታኖ ወደፊት ሲመለከት በቅርበት የሚታይ ምድር አለመኖሩን ተረዳና አፍሪካ በእርግጥም ሩቅ ነው ሲል አሰበ።

ሉዊ ጎጅ ለግዳጅ ሲጠራ ሚላን ውስጥ ከጓደኞቹ ጋር እየተዝናና ነበር። በብስክሌቱ ወደ ቤቱ በረረ እና ለቤተሰቦቹ እንዲሁም ለውዳጅ ጎረቤቶቹ ወደ አፍሪካ ሊሄድ መኾኑን ተናግሮ ተሰናበታቸው። ከምሽቱ ዐሥራ ኹለት ሰዓት ላይ ሚላን ባቡር ጣቢያ ሲደርስ በርካታ ወታደሮች እና ሸኚ ወዳጅ ዘመዶቻቸው አካባቢውን ሞልተውት ነበር።

«ቻዎ ማማ» በማለት ነበር ሊሸኙት የመጡ ቤተሰቦቹን ከባቡሩ ውስጥ ሆኖ የተሰናበታቸው። የእባቱ ዐይኖች በእምባ ሲሸፈኑ ተመለከተ። ወዲያውኑ ባቡሩ ጉዞውን ጀመረ። ጎጅ ወደ ኋላ ሲመለከት የሚላን ከተማ መብራት ቀስ በቀስ ሲደበዝዝ አየ። ከአንድ ምሽት የባቡር ጉዞ በኋላ ኔፕልስ የሚገኘው የጦር ሰፈር ደረሰ። ወዲያውኑ ወደ ኤርትራ የሚያደርገውን ጉዞ ጀመረ።








The *Minghetti* departs from Naples. From *L'Illustrazione italiana*, 2 February 1896.

**ምስል 5፡ ሚንጌቲ መርከብ ከኔፕልስ ስትነሳ (ጥር 2 ቀን 1896)**

ወደ ምፅዋ የተደረገው ጉዞ ዐሥራ ኹለት ቀናት ነበር የወሰደው። ለተለያየ የመንገድ ላይ ጨዋታ በቂ ጊዜ በመኖሩ ፖታኖ ከወታደሮቹ ጋር ስለሚሄድበት የጣሊያን ቅኝ ግዛት ኤርትራ የተለያየ ውይይት አደረገ። በውይይቱም ቀድሞ ስለ አፍሪካ የነበረውን አስተሳሰብ ቀየረ። ከጣሊያን ከመነሳቱ በፊት አፍሪካ በረኻማ እሲያም በርካታ አደገኛ አራዊትን በውስጡ የያዘ ጫካ መስሎት ነበር። ስለ ተራራማው ኤርትራ ነፋሻ አየር እና ተስማሚ መኖሪያነት ከጓደኞቹ ሲሰማ ተደሰተ።

የሜዲቴሪኒያን ባሕር መግቢያ የሆነው ስዊዝ ካናል ሲደርሱ ሰይድ ወደብ ላይ የነበረውን የጦፈ ገበያ ተመለከተ። በርካታ መርከቦች ዕቃ ይጭናሉ፣ ያወርዳሉ። ፖ ላይ የተሳፈሩ ወታደሮችም በገመድ ገንዘብ ለነጋዴዎች በማቀበል የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ አሳ፣ ዳቦ፣ መጠጥ እና ሲጋራ ገዝተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ሱዊዝ



The *Minghetti* departs from Naples. From *L'Illustrazione italiana*, 2 February 1896.

ምስል 5፡ ሚንጌቲ መርከብ ከኔፕልስ ስትነሳ (ጥር 2 ቀን 1896)

ካናልን ካለፉ በኋላ ጉዞአቸው አሰልቺ ነበር። ሙቀቱ ኃይለኛ በመኾኑ በርካታ ወታደሮች የጉዞአቸውን ወቅት በእንቅልፍ አሳለፉ።

ሉዊ ጎጂ እና ጓደኞቹ ምፅዋን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከቷት በጭለማ ነበር። የወደቧ አነስተኛ መብራቶች ከርቀት ይታያሉ። የበለጠ ሲቀርቡ ነበር የወደብ ከተማዋን ውበት የተመለከቱት። የከተማዋን ውበት ለማድነቅ በቂ ጊዜ ነበራቸው። በቅድሚያ ግን ጉዞ እና ሙቀት ያዳከማቸውን በቅሎዎቻቸውን ለማራገፍ ኹሉም መሯሯጥ ጀመሩ።

**ምፅዋ፡- የዘመናት ግዛት-እጤዎች ማዕከል**

ወደ ባሕር ዳርቻው ቀርቦ መኖር በምፅዋ ወሳኝ ነገር ነው። ለውኃው በቀረቡ መጠን የወደቧን ጤናማ እና ነፋሻ የባሕር ነፋስ ማግኘት ያስችላል። በምፅዋ ዳርቻ የሚታዩ ጥንታዊ ኪነ-ሕንፃዎች የግዛቷን ያለፈ ኃያልነት ያሳያሉ። ዕድሜ ጠገብ የኾኑ የባለጸጋ ቤቶች ከዳርቻው አንድ ማይል ርቀት ላይ በሚገኙ ደሴቶች ላይ የተገነቡ ሲኾኑ ከዋናው መሬት ጋር በእንጨት ድልድይ ይገናኛሉ። ከግራር እና አብደልቃድር ሰርጥ አጠገብ የሚገኙት ደሴቶች ጥንታዊ የመርከብ ግንባታ ቦታዎች እንደነበሩ ይገመታል።

በምፅዋ የሚገኙ የነጋዴ ቤቶች ከሌሎች ይለያሉ። ከተራው ማህበረሰብ ቤቶች ጎላ ብለው የሚታዩት ነጫጭ ቤቶች ባለ ረጃጅም መስኮቶች ሲሆን መስኮቶቹ በቂ ብርሐን እና ነፋሻውን የባሕር ንፋስ ያስገባሉ። ለዘመናት እንደታየው በርካታ ኃያላን ነገሥታት ሲነሱ እና ሲወድቁ ኖረዋል። በምፅዋ የባሕር ዳርቻ ለዘመናት በመኖር ላይ ያሉ የአረብ፣ የሕንድ እና የቱርክ የንግድ ማህበረሰብ፣ዘመን ለማይሽረው የንግድ ሥርወ-መንግሥት ቋሚ ምስክር ናቸው።

ዊርነር ሚዚንገር በግብፁ ንጉሥ እስማኤል ተሾሞ ምፅዋን ባስተዳደረበት የ1870ዎቹ ዓመታት ታውሉድ ደሴት ላይ ያስገነባው ቤተ-መንግሥት ከርቀት





ይታያል። ከግብፅ ቀጥሎ ጣሊያን ምፅዋን በ1885 ስትቆጣጠር ቤተ-መንግሥቱ እድሳት ተደርጎለት ‹‹ሴራግሊዮ ቤተ-መንግሥት›› የሚል ስያሜ ተሰጠው። ቤተ-መንግሥቱ በኢስታንቡል ቤተ-መንግሥታት መልክ የታነፀ ሲሆን ባለ ኹለት ፎቅ ቁመቱ እና ነጭ ቀለሙ ከርቀት እንዲታይ አስችሎታል። በሕንፃው ግራ እና ቀኝ የተገነቡ መወጣጫ ደረጃዎች ሲኖሩ ከአናቱ የሚታዩ ኹለት መብራቶችም አሉት።

ከሴራግሊዮ አጠገብ የሚገኘው ሌላ ሕንፃ በጣሊያን አስተዳደር የተገነባ የመኮንኖች ክበብ ነው። በርካታ የጣሊያን መኮንኖች በክበቡ በመገኘት በቀዝቃዛ መጠጥ ይዝናኑ ነበር። ከክበቡ ሕንፃ ጀምሮ እስከ ባሕሩ ዳርቻ የተዘረጋ የእንጨት ድልድይ ይገኛል። ክበቡ በምሽት የባሕር ዳርቻውን ውበት ለመመልከት በሚያስችል ሁኔታ ነበር የተገነባው።

ክበቡ ለተራ ወታደሮች አገልግሎት አይሰጥም ነበር። ተራ ወታደሮች ግራር እና አብድል ቃድር ላይ እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር። ለመካከለኛው ምሥራቅ ወደቦች ካላት ቅርበት የተነሣ በምፅዋ ‹‹የጣሊያን፣ ፈረንሳይ፣ ግሪክ፣ ሕንድ፣ ግብፅ፣ ሱዳን፣ አረብ፣ ኑቢያ፣ ሶሪያ፣ አርሜኒያ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን እና የሌሎች በርካታ አገራት የንግድ ሰዎች ይገኛሉ›› በማለት ሴዛር ፒኒ ጽፎ ነበር።

በምፅዋ የነበሩ ወታደሮች ከአለቆቻቸው በርካታ እገዳ ይደርስባቸው ነበር። ለምሳሌ ያህልም ወታደሮቹ ባሕር ዳርቻው ላይ ገላቸውን እንዳይታጠቡ ይከለከሉ ነበር። የተለያየ የቆዳ በሽታ ሊይዛቸው እንደሚችልም አለቆቻቸው ያስጠነቅቋቸው ነበር። በዚህ የተነሣም በምፅዋ የነበሩ ወታደሮች በባሕር ዳርቻው ከሚገኙ የግሪክ ሻይ ቤቶች ሌላ ስለከተማዋ ብዙ ዕውቀት አልነበራቸውም።

በ1880ዎቹ በምፅዋ የሚገኙ ኹለት ካፍቴሪያዎች ለጣሊያን መኮንኖች እንደ ጽሕፈት ቤት ያገለግሉ ነበር። በ1885 የጣሊያንን መምጣት ተከትሎ ኹለቱ የግሪክ ሻይ ቤቶች ካፌ ሞንቴቤሎ እና ካፌ ጋሪባልዲ በሚል ተሰየሙ። ባለቤቶቹ

ግሪካውያንም አውሮፓዊ ደንበኞቻቸውንም ሆነ የአገሬውን ሰው ላለማስቀየም በካፍቴሪያቸው ላይ የየትኛውንም አገር የዘላይነት የሚያሳዩ ምልክቶችን ላለማሳየት ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። ብዙም ሳይቆይ በ1880ዎቹ መገባደጃ ላይ ጣሊያንኛ ከአረብኛ ጋር በመፎካከር የምፅዋ የንግድ መግባቢያ ቋንቋ ለመሆን ቻለ።

በምፅዋ ታዋቂ ባለጸጋ ነጋዴ የነበረው ጣሊያናዊው አሌሳንድሮ ሴሮር ነበር። በጣሊያን ሊቮርኖ ከአይሁድ ቤተሰቦቹ የተወለደው ሴሮር በመጀመሪያ ያቀናው ወደ ካይሮ ነበር። በግብፅ ቆይታው ከሕዝብ ጋር ለመቀራረብ እንዲረዳው በማሰብ ለራሱ «እስክንድር» የሚል የቁርክ ስም አወጣ። በመቀጠል ወደ ምፅዋ የመጣው በእንቁ ንግድ ላይ ለመሰማራት አስቦ ነበር። በምፅዋ ቆይታው እስክንድር ሴሮር በሚል ስሙ ይታወቅ የነበረ ሲሆን በአንዳንዶች ዘንድ «እንቁ ነጋዴው» ተብሎ ይጠራ ነበር።

ከጣሊያኖች መምጣት በፊት ሴሮር በተለምዶ የምፅዋ ከንቲባ እንደሆነ ይነገርለት ነበር። የአገሩ ሰዎች የወደብ ከተማዋን ከተቆጣጠሩ በኋላም የሴሮር የእንቁ ንግድ አልተቋረጠም ነበር። በምፅዋ በርካቶች ከወገባቸው በላይ እራቁታቸውን በሚንቀሳቀሱበት የበጋ ሙቀት ሴሮር ሙሉ ልብሱን ለብሶ ነበር የሚዘዋወረው።

በምፅዋ የጣሊያኖች የመጀመሪያ እግር መርገጫ የነበረው መሬት ከአራት ስኩዌር ማይል አይበልጥም። በጠባቧ ቦታ የተጀመረው የጣሊያን የግንባታ እንቅስቃሴ በፍጥነት ነበር ምፅዋን ያዳረሰው። የባሕር ዳርቻውን በአዲስ መልክ ገነቡት፣ በመቀጠልም ሆስፒታል፣ የጦር መሣሪያ እና የማቀዝቀዣ ፋብሪካዎችን አቆሙ። ምፅዋን ከተራራማው የመሐል ኤርትራ ግዛት ጋር የሚያገናኝ የባቡር ሃዲድም የተገነባው በተመሳሳይ ወቅት ነበር።

በምፅዋ የንግድ እንቅስቃሴ ማደጉን ተከትሎ በርካታ አውሮፓውያን ወደ ቀይ ባሕሯ ወደብ መጡ። በምፅዋ ምንም ዓይነት መጠለያ ዛፍ ያልነበረ ሲሆን በርካታ ሻይ ቤቶች እንደ መጠለያም እንደ መዝናኛም ማገልገል ጀመሩ። ቀን ቀን ከተማዋ





ፍጹም ፀጥታ የሚሰፍንባት ስትሆን የተለየ እንቅስቃሴ ለማድረግ ሙቀቱ አስቸጋሪ በመኾኑ ሰዎች በቤታቸው ነበር የሚያሳልፉት።

ምፅዋ በደበልጥ የምትታወቅባቸው ኹለት ማዕከላዊ ቦታዎች ወይም በተለምዶ ፒያሳ ነበሯት። ቦታዎቹን ባራቴሪ እና ሰንአፊ በማለት በ1895 ነበር ጣሊያኖች ስያሜ ያወጡላቸው። በፒያሳዎቹ ያሉ የንግድ ማዕከላት የማን እንደኾኑ ከአሠራራቸው በቀላሉ መለየት ይቻል ነበር። የሕንድ ሱቆች ጣሪያቸው አጭር ሲሆን የብረት በር አላቸው። ግሪኮች፣ አረቦች እና ሕንዶች በወርቅ ማንጠር ሥራ ላይ የተሰማሩ ነበሩ። በአብዛኛው የሚያመርቱትን የወርቅ ጌጣጌጦች ለአረብ እና አቢሲኒያ ገበሬዎች ያቀርቡ ነበር።

በወቅቱ አዲስ በተከፈተው ካፌ ኦሪየንታሌ ዙሪያ በርካታ የመንገድ ላይ ነጋዴዎች ይርመሰመሱ ነበር። የሕንድ ሱቅ በደረቴዎች የተለያዩ አልባሳትን፣ ኮፍያ እና ጌጣጌጦችን ሲሸጡ ጥቁር አፍሪካውያን ደግሞ ሲጋራ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ሎሚ እና የተለያዩ ፍራፍሬዎችን ያዞሩ ነበር። በአካባቢው የነበሩ የአረብ ነጋዴዎች አነስተኛ ዳስ በማቆም የተለያዩ ጌጣጌጦችን፣ ሽቶዎችን እና እጣን ይሸጡ ነበር። የገበያው አካባቢ በተለያዩ ፍራፍሬዎችና ቁሳቁሶች ሽታ የተሞላ ሲሆን በተለይ በከፍተኛ ጫጫታው ይታወቅ ነበር።

ካፌ ጋሪባልዲ በዘመኑ ታዋቂ የመዝናኛ ሥፍራ ነበር። የተለያዩ የአገሬው አዝማሪዎች ጣሊያናውያኑን በዘፈናቸው ያዝናኑ ነበር። በወቅቱ ዝነኛ የነበሩ የጣሊያንኛ ዜማዎች ይዘፍኑ የነበሩ ሲሆን *«ላ ኢታሊያ ሬስታ ኢን አፍሪካ»* የተባለው የጣሊያንኛ ዘፈን ተወዳጅ ነበር። ዘፈኑ ጣሊያን በአፍሪካ ስለሚኖራት ቆይታ እየነሳ የሚያሞግስ ነበር። ከካፌ ጋሪባልዲ ሌላ ደግሞ አቅሙ የነበራቸው ግለሰቦች የሚዝናኑበት ዲና ካርሚላ የተባለ መጠጥ ቤት ነበር።

በወቅቱ የነበረውን የጣሊያን ወታደራዊ እንቅስቃሴ እና የውጪ ዜጎች መበራከት ተከትሎ በምፅዋ ሴተኛ አዳሪነት ተጀመረ። በመጀመሪያ የነበሩት የቱርክ፣ የጥቁር አፍሪካ እና የግብፅ ሴተኛ አዳሪዎች ብቻ ሲኾኑ የጣሊያን ወታደሮችን መበራከት ተከትሎ በርካታ የምፅዋ ሴቶችም የወሲብ ንግዱን ተቀላቀሉ።

አጠቃላይ የንግድ ምክር ቤት ባይኖራትም ምፅዋ ታላቅ የንግድ ማዕከል መሆን ችላ ነበር። የቀይ ባህሯ እንቁ የሚል ስያሜን ማግኘት የቻለችውም በዚሁ የንግድ እንቅስቃሴዋ ነበር።





# ምዕራፍ ሦስት

# ጣሊያን በአፍሪካ

የታሪክ ምስክር መገኛ ቤተ-መዛግብት እና ሙዚየሞች ብቻ አይደሉም። አንዳንድ ጊዜ የምንረግጠውም መሬት የታሪክ ምስክር ሊሆን ይችላል። በሮም የሚገኘው ቺንኲቼንቶ አደባባይም የዚህ ማሳያ ነው። የአደባባዩ ስም «የአምስት መቶዎች አደባባይ» የሚል ትርጓሜ አለው። አደባባዩ የ1500ዎቹን የጣሊያን የሕዳሴ ዓመታት ወይም ደግሞ ከኹለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የአውሮፓን ገበያ ተቆጣጥሮ የነበረውን የፊያት ቺንኲቼንቶ ሞዴል ለመዘከር አይደለም የተሰየመው።

«አምስት መቶዎች» ጣሊያን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አፍሪካ ዘምታ ድል በተነሳችበት ወቅት የሞቱ ወታደሮቿን የሚዘክር አደባባይ ነው። ወታደሮቹ የሞቱት ዶጋሊ ላይ በተደረገ ፍልሚያ ወቅት ነበር።

የዶጋሊውን ዘመቻ የጀመረው በመንኮታኮት ላይ የነበረው የኦቶማን ቱርክ መንግሥት ነበር። መንግስቱም እስማኤል አንደኛ የተባሉ ንጉሥ ይመሩት የነበረው ዐሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በጅቡቲ እና ሱዳን መካከል የሚገኘውን የቀይ ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ሰፊ ግዛት በሥሩ አድርጎ ነበር። በግዛቱ የነበረው የቱርክ አስተዳደር ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል መዝለቅ ችሎ ነበር።

እስማኤል ፓሻ የግብፅ ንጉሥ ምክትል በመሆን በ1867 ከተሾሙ በኋላ ግብፅን በአውሮፓ መልክ የመገንባት እንቅስቃሴ ጀመረ። ካይሮን አፍርሶ በፓሪስ መልክ ለመገንባትም መንቀሳቀስ የጀመረው የሹመት ፊርማው ሳይደርቅ ነበር።

የስዊዝ ካናል በ1869 መከፈቱን ተከትሎ የቀይ ባሕር ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ጨመረ። ይሄንን የተመለከተው እስማኤል ፓሻም የግብፅን ግዛት ወደ

ደቡብ ለማስፋት በማሰብ ኢትዮጵያንና እና ሱዳንን ለመውረር ተዘጋጀ። የዓባይ ወንዝ መነሻ የሆነችውን ኢትዮጵያንም በመያዝ ግብፅ የቀይ ባሕርን የንግድ መሥመር እና የዓባይ ሸለቆን በበላይነት የምትቆጣጠርበትን ዕቅድ አወጣ።

የወረራ እንቅስቃሴውን የጀመረው ሱዳን ላይ ሲሆን በዳርፉር ጊዜያዊ አስተዳደሩን በ1874 አቋቋመ። ወደ ኢትዮጵያ በማቅናትም ሐረርን በ1875 ተቆጣጥሮ ለቀጣይ እንቅስቃሴ ዝግጅቱን አፋጠነ። የእስማኤል ቀጣይ እንቅስቃሴ የተገታው የኢትዮጵያ ሠራዊት በ1876 ጉራ ላይ እና በ1883 ደግሞ ሰአቲ ላይ ባደረሰበት ከፍተኛ ጥቃት ነበር።

እስማኤል ግብፅን በዘመናዊ መልክ ለመገንባት የነበረው ሕልም ከገንዘብ ዐቅሙ ጋር አይመጣጠንም ነበር። በመኾኑም የአውሮፓ የብድር አቅርቦት አስፈለገው። አበዳሪ አውሮፓውያንም ለግል ጥቅማቸው ሲሉ የግብፁ ንጉሥ አውሮፓዊ አማካሪዎችን እንዲቀጥሩ ቅድመ ሁኔታ አቀረቡ። ይሄንን ተከትሉም የእስማኤል ፓሻ ስልጣን ቀስ በቀስ ተሸረሸረ።

በ1870ዎቹ እና 80ዎቹ በቀይ ባሕር ዳርቻ እና መሐል አገራት የነበረው የግብፅ አስተዳደር መዳከም ጀመረ። በሱዳን የነበረው የግብፅ አስተዳደርም በሞሃመድ አህመድ ከሚመራው የእስላማዊው ፀረ-ቅኝ ግዛት ቡድን «መሃዲስት» ብርቱ ተቃውሞ ገጠመው። ተቃውሞው በተለይም በእንግሊዝ ይተዳደር የነበረው ምዕራባዊ ሱዳን የበለጠ ተጠናክሮ ቀጠለ።

በነበረው ከፍተኛ የሰበካ እና የንግግር ችሎታው በመታገዝ ሞሃመድ አህመድ በርካታ ሱዳናውያን የመሃዲስት እንቅስቃሴውን በመቀላቀል በግብፅ እና እንግሊዝ ኃይሎች ላይ እንዲነሱ ማድረግ ቻለ። በ1881 ወደ ሙሉ ጥቃት በመሸጋገርም የእንግሊዝ እና ግብፅ የጋራ የጦር ሰፈሮች ላይ እርምጃ መውሰድ ጀመረ። በወርኃ ጥቅምት በ1883 በኮሎኔል ዊሊያም ሂክስ የሚመራውን ጦር ደመሰሱ። በመቀጠልም





ካርቱምን ከመሃዲስቶች ለመጠበቅ የተሳከው የጀነራል ቻርልስ ጎርደን ጦር ተፈታ። በመጨረሻም መላዋ ምዕራብ ሱዳን በመሃዲስት ቁጥጥር ሥር ዋለች።

እንግሊዝ ከመሃዲስት ጋር ለምታደርገው ትግል የኢትዮጵያ አጋርነት የግድ አስፈልጓት ነበር። የእንግሊዝ ጦር መሃዲስት ከሰሜን አቅጣጫ በሚያጠቃበት ወቅት ኢትዮጵያ ምሥራቁን ክፍል ብትቆጣጠር ድል ማስመዝገብ እንደሚቻል እንግሊዝ አሰላች። በመቀጠልም በ1883 አድሚራል ሥር ዊሊያም ሄዊትን ወደ አድዋ በመላክ አፄ ዮሐንስን በቀላሉ ለማሳመን ቻለች።

አፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያ ውስጥ የመሃዲስት ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳይፈጠር ባደረባቸው ስጋት የተነሣ ነበር የእንግሊዝን ጥያቄ በፍጥነት የተቀበሉት። ከአገር ውስጡ ስጋታቸው ሌላ በሰሜን የአገሪቱ ክፍል ያለውን የሱዳን እና የግብፅ ተፅዕኖ በመቀነስ የምፅዋ የባሕር በራቸውን የማስከበር ዓላማም ስለነበራቸው የእንግሊዝ ጥያቄ ወቅቱን የጠበቀ ሆኖላቸዋል።

በዚያ ወቅት ምፅዋ ትተዳደር የነበረው በግብፅ ሲሆን ግብፅም አሜሪካዊው አሌክሳንደር ማኮብ ማሰን በአስተዳዳሪነት ቀጥራው ነበር። ወቅቱ ምፅዋ ታላቅ የንግድ ማዕከል የሆነችበት ዘመን ነበር። መነሻቸውን ምጽዋ ያደረጉ ነጋዴዎች ሱዳንን አቋርጠው ወደ ምዕራብ አፍሪካ ያልፉ ነበር። በንግድ መርከቦችም የሚጫኑ ዕቃዎች ወደ አረብ አገራትና ሕንድ የሚሄደው ከምፅዋ በመነሳት ነበር። ኢትዮጵያ በምፅዋ የመጠቀም መብት እንዳላት በመጥቀስ አፄ ዮሐንስ ጦራቸውን እንደሚያዘምቱ የተናገሩበት ወቅትም ነበር። በዚያን ጊዜ የግብፅ ተወካይ የነበረው ማሰን ኢትዮጵያ ምፅዋን መጠቀም እንደምትችል ነገር ግን የባለቤትነት ጥያቄ ማንሳት እንደሌለባት በንቀት የተሞላ መልስ ሰጥቷቸው ነበር።

በሰኔ 1884 አድዋ ላይ የተገናኙት ሰር ዊሊያም ሄዊት፣ አፄ ዮሐንስ እና አሌክሳንደር ማኮብ ማሰን በተለምዶ "የሄዊት ስምምነት" ተብሎ የሚጠራውን የጋራ

ስምምነት ተፈራረሙ። ስምምነቱ አፄ ዮሐንስ በመሃዲስት ተቃዋሚዎች ላይ ወታደራዊ ተፅዕኖ በማድረግ ሱዳን ውስጥ የታፈኑትን የግብፅ ወታደሮች እንዲያስለቅቁ ያዛል። በምላሹ ደግሞ እንግሊዝ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኘው የቦጎስ ግዛት የኢትዮጵያ ግዛት አካል ለመኾኑ ዕውቅና እንደምትሰጥ በስምምነቱ ሰፍሯል። በተጨማሪም ማሰን እና እንግሊዝ ኢትዮጵያ ወጪ እና ገቢ ንግዷን በምፅዋ በኩል እንድታከናውን የሚያስችላትን ዋስትና ለመስጠት ተስማሙ።



[illegible] IV. From Lincoln de Castro, Nella terra dei negus, pagine [illegible] Milan: Fratelli Treves [illegible]

***ምስል 6፦ አፄ ዮሐንስ አራተኛ***





የሄዊት ስምምነት የፊርማ ቀለም ከመድረቁ በፊት ነበር አለመግባባት የተፈጠረው። በሐምሌ ወር ለአፄ ዮሐንስ የሚደርስ 50 ሳጥን የጦር መሣሪያ የጫነችው ኮርሲካ የንግድ መርከብ ምፅዋ ደርሳ ጭነቷን አራገፈች። የወደቡ አስተዳዳሪዎች መሣሪያው እንዳያልፍ አገዱ። በወቅቱ ለነበረው የወደቡ አስተዳዳሪ አሜሪካዊው ማሰን ድርጊቱን በመኮነን ደብዳቤ የጻፉት የአፄ ዮሐንስ የጦር መሪ የነበሩት ራስ አሉላ ናቸው። ከሦስት ወራት በኋላ ጥቅምት 1883 ላይ አፄ ዮሐንስ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ያዘለ ደብዳቤ ለማሰን ፃፉ። በደብዳቤያቸውም በሄዊት ስምምነት መሠረት ጦራቸውን ወደ ሱዳን ለመላክ የተዘጋጁ ቢሆንም የማሰን አካሄድ ግን ስምምነቱን የሚጥስ መኾኑን ጠቀሱ። ንጉሡ አያይዘውም ጦራቸውን ወደ መሃዲስት ከማዝመት ይልቅ በቀጥታ ወደ ምፅዋ እንደሚልኩ ዛቱ።

### የግብፅ በር ከፋችነት እና የጣሊያን አገባብ

የካቲት አምስት ቀን 1885 ዓ.ም በጋሪባልዲ የሚመሩትን 800 የጣሊያን ወታደሮች ያሳፈረችው አሜዲዮ መርከብ አመሻሽ ላይ ምፅዋ ደረሰች። በወቅቱ ምፅዋን የሚያስተዳድረው የግብፅ ሠራዊት ቦታውን ለጣሊያን ለመልቀቅ በዝግጅት ላይ ነበር። በምፅዋ ቤተ-መንግሥት የጣሊያን እና የግብፅ ባንዲራ ጎን ለጎን ተሰቅሎ አስተዳደራዊ ሽግግር መደረጉ ታወጀ። ለምፅዋ ነዋሪዎች በተነገረው ዐዋጅ መሠረት ከእንግሊዝ፣ ቱርክ እና ግብፅ መንግሥታት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው የጣሊያን መንግሥት የወደብ ከተማዋን እንደሚያስተዳድራት አሳወቀ።

የናፒየር ዘመቻ እና የቤልጅየሙ ንጉሥ ሊዮፓልድ ኮንጎን የመያዝ ስኬት በመመልከት ጣሊያን ኢትዮጵያን በቀላሉ መያዝ እንደምትችል የልብ ልብ ተሰማት። የጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶም የቤልጅየምን ፈለግ በመከተል ሸዋ አካባቢ ሌት ማረፊያ በተባለ ቦታ በጣሊያን የጂኦግራፊ ማህበር ስም ሳይንሳዊ ማዕከል ገነቡ። በመቀጠልም በ1881 እና በ1883 በጁሲፔ ጉሊቲ እና ጎስታቮ ቢያንቺ የተመሩ አገር አሳሾችን ወደ መሃል ኢትዮጵያ ለማስገባት ሞከሩ።



...hannes IV. From Lincoln de Castro, *Nella terra dei negus, pagine racc...*
...*lte*. Milan: Fratelli Treves, 1915.

ምስል 6፡- አፄ ዮሐንስ አራተኛ

የአሳሾቹ ሙከራ በእንጭጩ የተቀጨው ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ከመጠጋታቸው በፊት አባላቱ በሙሉ በመገደላቸው ነበር። የአሳሾቹ ግድያም ለተወሰነ ጊዜ የኢትዮጵያን ግዛት ከተመሳሳይ ሰርጎ ገቦች ለመከላከል ቢያስችልም በይዘቱም ሆነ በኃይል አሰላለፉ ከፍተኛ ከሆነ ቀጣይ ወረራ በዘላቂ ሊጠብቃት አልቻለም ነበር።

የአሳሾቹን መገደልን ተከትሎ ኢትዮጵያ ለዜጎቿ በቂ የደኅንነት ጥበቃ ባለማድረጓ ጣሊያን ወቀሰች። በመቀጠልም በቀጠናው ያሉ «ዜጎቿን እና ጥቅሟን ለማስጠበቅ» በሚል ሽፋን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራዊቷን ወደ ኢትዮጵያ ማስጠጋት ጀመረች። የጣሊያት የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ፓስኳል ስታኒስላኦ ማንሲኒ በጥር 1885 በቱርክ ከነበረው የጣሊያን አምባሳደር ጋር ባደረጉት የቴሌግራፍ ልውውጥ «የአገራቸውን ጥቅም እና ክብር ለማስጠበቅ» ጣሊያን ወታደሮቿን ወደ ኢትዮጵያ እንደምትልክ ገልጸው ነበር። ከጥቂት ቀናት በኋላም በምፅዋ የነበረው የግብፅ አስተዳደር በጣሊያን ተተካ።

## የጣሊያን ወደ ተራራማው የኢትዮጵያ ግዛት መጠጋት

እንግሊዝና ግብፅ በሄዊት ስምምነት አፈፃፀም ላይ ባሳዩት ልግመኝነት አፄ ዮሐንስ ተቆጥተው ነበር። ስምምነቱ ኢትዮጵያ የምፅዋን ወደብ መጠቀም እንድትችል በማመቻቸቱ የተደሰቱት አፄ ዮሐንስ ቀስ በቀስ ወደቡን ሙሉ በሙሉ መልሰው እንደሚያገኙ ተስፋ አድርገው ነበር። በፊርማው ወቅትም ምፅዋ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ አስተዳደር እንደምትዘዋወር በማመን ነበር የግብፅ ቆይታ ላይ ያላንገራገሩት።

የእንግሊዝ ተወካዮች በበኩላቸው ከስዊዝ ካናል መከፈት በኋላ በቀይ ባሕር ላይ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታዋ የጎላውን ምፅዋ ለዮሐንስ መስጠቱ አላስተማመናቸውም ነበር። ለዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ ፈረንሳይ ምፅዋን ከጅቡቲ ጋር በመቀላቀል ከያዘች እንግሊዝ በቀይ ባሕር አካባቢ የሚኖራትን የበላይነት በቀላሉ ልታጣ ትችላለች የሚለው ፍራቻ ነበር።





የግብፅን መልቀቅ ተከትሎ እንግሊዝ ምፅዋን ለጣሊያን ያሸጋገረችው ወደቡ በኢትዮጵያ እጅ ቢመለስ በቀላሉ ፈረንሳይ ልትወስደው እንደምትችል በመፍራት ነበር። ጣሊያን የእንግሊዝ ታማኝ ወዳጅ ባትሆንም በምፅዋ መቀመጧ ወደቡን ከፈረንሳይ ስጋት ነፃ ያደርገዋል። ምክንያቱም በበርሊኑ ጉባዔ ላይ አንድ አውሮፓዊ አገር የያዘውን ቅኝ ግዛት ሌላ አገር እንደማይነጥቀው የተደረገ ስምምነት ነበር።

በቀይ ባሕር አካባቢ የእንግሊዝ ተወካይ የነበረው አጉስቶስ ዋይልድ ስለ ወቅቱ ሁኔታ ሲናገር፦ «እንግሊዝ አፄ ዮሐንስ ከተጠቀመችባቸው በኋላ ለጣሊያን አሳልፋ በመስጠት ከፍተኛ ክህደት ፈፅማለች» ብሎ ነበር። አፄ ዮሐንስ በድርጊቱ ቢናደዱም በቀጥታ ወደ ምፅዋ ለመዝመት አልወሰኑም። ተጨማሪ እንቅስቃሴ ለማድረግ እስካልሞከረች ድረስም የጣሊያንን በምፅዋ መኖር እንደማይቃወሙ ከጣሊያን ተወካይ ጋር በተገናኙበት ወቅት ተናግረው ነበር።

ይሄንን ተከትሎ ከ1886 እስከ 1887 ባሉት ወራት ጣሊያን ከምፅዋ በመነሳት ወደ መሃል ኢትዮጵያ መጠጋት ጀመረች። ጣሊያን ሰአቲ ላይም ምሽግ በመገንባት ለቀጣይ ወረራ መዘጋጀት ስትጀምር በራስ አሉላ ከሚመራው ጦር ጋር ጥር 25 ቀን ፊት ለፊት ተገናኘች። የኹለቱን ፍጥጫ የተለየ የሚያደርገው በመጠኑ የታጠቀ አፍሪካዊ ጦር ከተደራጀ የአውሮፓ ኃይል ጋር መግጠሙ ነበር። በውጤቱ የኢትዮጵያ ጦር ብርቱ ጉዳት ሲደርስበት ከመድፈኛው የጣሊያን ጦር ግን አንድም ወታደር አልቆሰለም ነበር።

በሚቀጥለው ቀን ዕድል ፊቷን ወደ ኢትዮጵያ አዞረች። የሰአቲውን ምሽግ ለማጠናከር በኮሎኔል ቶማሶ ክሪስቶፋሪስ የሚመራ 540 የጣሊያን እና አምሳ የኤርትራ ተወላጆችን የያዘ ጦር ከምፅዋ ወደ ሰአቲ በመንቀሳቀስ ላይ መኾኑን ራስ አሉላ ደረሱበት። ከአንድ ቀን በፊት የደረሰባቸውን ሽንፈት ለመበቀልም አጋጣሚውን ለመጠቀም ወሰኑ።

ከምፅዋ እስከ ሰአቲ ያለው መንገድ በስንሰለታማ ጉብታ እና ቁጥቋጦ የተሸፈነ ሲሆን መልክአ ምድሩን በመጠቀም የጣሊያንን ጦር ለመቁረጥ አቀዱ። በዘመቻ ዕቅዱም መሠረት ጥቂት ወታደሮቻቸውን ለእይታ ከጣሊያን ሠራዊት ፊት በማሰለፍ ቀሪ አምስት ሺህ ወታደሮቻቸውን በተራራው ላይ እንዲመሽጉ አደረጉ።

የጣሊያን ሠራዊት ከእይታ ሲገባ የአሉላ ጦር ከሦስት አቅጣጫ ተኩስ ከፈተ። የጣሊያን ወታደሮች ምንም ዓይነት የመልስ ተኩስ ሳያደርጉ በአሉላ ሠራዊት ተሰቀሙ። ሁኔታውን የተመለከተው ኮ/ል ክሪስቶፎሪስ ጥቂት የተረፉ ወታደሮቹን አስከትሎ ወደ ኋላ በማፈግፈግ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ተራራ ወጣ።

ኰሉኔሉ ወታደሮቹን በታ ለማስያዝ በመዘጋጀት ላይ ሳለ ነበር በአሉላ ሠራዊት መከበቡን ያወቀው። በቀጣይ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከሰማንያ በላይ የጣሊያን ወታደሮች በተራራው ላይ ተገደሉ። ዘመቻውን የኢትዮጵያ ወታደሮች ሲገልጹት «ወደ ሰርግ የመሄድ ያህል ነበር» ብለዋል።

በአሉላ አስገራሚ የዘመቻ ዕቅድ የጣሊያንን ጦር ዶጋሊ ላይ ሙሉ በሙሉ የደመሰሱት የኢትዮጵያ ወታደሮች ግስጋሴያቸውን በመቀጠል እስከመጨረሻው እንዲቀጥሉ አዝማቻቸውን ጠየቁት። ራስ አሉላም ትንሽ አቅማምቶ በመጨረሻ አካባቢውን ለቆ ተመለሰ።

በዶጋሊው ድንገተኛ የአሉላ ወረራ ወቅት በርካታ የጣሊያን ወታደሮች በአግራሞት ቆመው ኢትዮጵያን ሠራዊት ከመመልከት ውጪ አልተንቀሳቀሱም ነበር። በርካታ የአውሮፓ ጋዜጦች የዶጋሊን አስገራሚ ገድል የዶጋሊን የጦርነት ውሎ ንጉሥ ሊዮኒደስ ሦስት መቶ የስፓርታ ወታደሮችን በመያዝ ከወራሪው የፐርሺያ ጦር ጋር ከተፋለመበት ታሪካዊ ክስተት ጋር በማመሳሰል ዘግበዋል። ኹለቱን ታሪኮች የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር ሦስት መቶ የስፓርታ ሠራዊት እና አምስት መቶ የጣሊያን ወታደሮች ሙሉ በሙሉ መሞታቸው ነበር። ከዚህ ሌላ ግን ስፓርታውያኑ አገራቸውን ከወራሪ ለመከላከል የዘመቱ ሲኾኑ ጣሊያውያኑ ግን የሰው አገር ለመውረር ባደረጉት ሙከራ ላይ ነበር ያለቁት።








*ምስል 7፦ የዶጋሊ ውሎ (የላ ትሪቡና ላይ የተወሰደ፤ ጥር 26 ቀን 1895)*

የዶጋሊውን ክስተት የሰሙት የሮም ነዋሪዎች አምስት መቶ የተሰዉ ወታደሮቻቸውን ለማሰብ ለክብራቸው አደባባይ እንዲሰየምላቸው ጠየቁ። ከሮም ዋናው የባቡር ጣቢያ አጠገብ የሚገኘው ቺንኲቼንቶ አደባባይም ለአምስት መቶዎቹ ለማዕታት መታሰቢያ ሆኖ ከተገነባ በኋላ ሰኔ 5 ቀን ስያሜው ጸደቀ።

ዶጋሊ ላይ በግፍ ለተገደሉባት አምስት መቶ ወታደሮች ካሳ የሚሆን ግዛት ኢትዮጵያ እንድትሰጣት ጣሊያን ጥያቄ አቀረበች። የጣሊያንን ጥያቄ በምንም ዓይነት እንደማይቀበሉት በመጥቀስ አፄ ዮሐንስ ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ ላይ አስታወቁ። በደብዳቤያቸው ጨምረው እንደገለጹት የዶጋሊው ጦርነት የተከሰተው እንግሊዝ የሄዊት ስምምነትን ባለማክበሯ መኾኑን በመጥቀስ ወቅሰዋል።

በርካታ አውሮፓውያን ራስ አሉላ አነስተኛ ቁጥር የነበረውን የጣሊያን ጦር መማረክ ሲችል በግፍ መግደሉ ትክክል አለመኾኑን በመጥቀስ ወቅሰው ነበር። አፄ



The Legend of Dogali. From *La Tribuna Illustrata*, 26 January 1895.

ዮሐንስም አሉላን በመከላከል ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብዳቤ ጀነራላቸው አገሩን ከወራሪ ከመከላከል ውጪ ማንም አገር ላይ ጥቃት አለመፈጸሙን ተናግረው ነበር። ከኹለቱ ወገን የሚነሳው ወቀሳ እና ምላሽ እንዳለ ሆኖ የዶጋሊው ምላሽ አንድ መንግሥት አገሩን ከወራሪ ለመጠበቅ የሚወስደው የመከላከል እርምጃ እንደነበር ግልጽ ነው።

ሮም የነበሩት ሰር ጆን ሳቪል ለእንግሊዝ ንግሥት በጻፉት ደብዳቤ ጣሊያን ዶጋሊ ላይ ለተፈጸመባት ግፍ ካሳ እንደምትፈልግ በተደጋጋሚ እየገለጸች መሆኗን አሳወቁ። ኢትዮጵያ አስፈላጊውን ካሳ የማትከፍላት ከሆነ ሐያ አምስት ሺህ ወታደሮችን በመላክ ራስ አሉላን ለመቅጣት እየዛተች መሆኗንም ሳቪል ጠቁመው ነበር። በደብዳቤያቸውም ጣሊያን ራስ አሉላን ፍለጋ ወደ መሃል ኢትዮጵያ የምትዘምት ከሆነ የዶጋሊ ዓይነት ሁኔታ ሊጠብቃት እንደሚችል እንዲሁም ራስ አሉላን መያዝ ያለው ጠቀሜታ እንዳልታያቸው አሳስበውም ነበር።

ንግስፈራሪያዋ በተጨማሪ ጣሊያን በኢትዮጵያ ድንበር ላይ ያላትን ይዞታ በማስፋት ከኢትዮጵያ ጋር የንግድ ግንኙነቷን በማጠናከር የኢትዮጵያን ምርቶች ለመግዛት አቅዳለች። አካሄዷ አጠራጣሪ ዓላማን ከጀርባው የያዘ ካልሆነ በስተቀር ለጣሊያን ታላቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ጥሬ ዕቃ ኢትዮጵያ አታመርትም። በተጨማሪም የጣሊያን ሕዝብ የመንግሥታቸውን የመስፋፋት እርምጃ አይደግፍም በማለት ነበር ሰር ጆን ሳቪል የጣሊያንን የወረራ ዕቅድ አገራቸው እንግሊዝ እንድታስብበት ያስጠነቀቁት።

እንግሊዝም ካይሮ በነበረው ቋሚ መልዕክተኛዋ ጀራልድ ፖርታል የሚመራ የዲፕሎማቶች ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ላከች። ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቷን ለኢትዮጵያ ላለማሳወቅ ፖርታል ባለሙሉ ሥልጣን መልዕክተኛ እንዳልሆነ በሹመት ደብዳቤው ላይ ጠቅሳ ነበር። ዕድሜው በሐያዎቹ አጋማሽ የሚገኘው ፖርታል በኢቶን ዩኒቨርስቲ የዲፕሎማሲ ትምህርት የቀሰመ ሲሆን የኢትዮጵያ ተልዕኮውን በከፍተኛ





ጉጉት ነበር የተቀበለው። በጉዞው ወቅት ኹሉንም እንቅስቃሴ እና ክስተት በጉዞ ማስታወሻው ያሰፈረ ሲሆን በኋላም በእንግሊዝ ተወዳጅ ከኾኑ የጉዞ እና አሰሳ ታሪኮች ጋር አብሮ አሳትሞታል።

የፖርታል ተልዕኮ ከመጀመሪያው ነበር እንቅፋት የበዛበት። ከሄዊት ስምምነት በኋላ እንግሊዝ ላይ ዕምነት ያጡት አፄ ዮሐንስ ፖርታል የሚመራው የዲፕሎማቶች ቡድን የጣሊያንን የጦር ጉዳት ካሳ ጥያቄ ለማስፈጸም የመጣ ስለመኾኑ ተጠራጠሩ። በንግሥት ቪክቶሪያ ማኅተም ለአፄ ዮሐንስ የተላከው ደብዳቤም የንጉሡን ጥርጣሬ አጠናከረው። ደብዳቤው «ጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ ዘልቃ የገባችው ነጋዴ ዜጎቿን ለመጠበቅ ሲሆን የራስ አሉላ ጥቃትም ይሄንን ያላገናዘበ ነበር» በማለት እንግሊዝ ለጣሊያን ያላትን ወገንተኛነት ያሳየ ነበር።

ፖርታል በጥቅምት 1887 ወደ ምፅዋ በማምራት ነበር ተልዕኮውን የጀመረው። በምፅዋ ቆይታው የጣሊያንን የጦር ጉዳት ካሳ ጥያቄ በዝርዝር ተቀበለ። በጥያቄዋ መሠረትም ጣሊያን ዶጋሊ[1] ሰአቲ እና ሌላም በአቢሲኒያ ግዛት ሥር ያልኾኑ ቦታዎች እንዲሰጧት ዘረዘረች። የጣሊያንን ጥያቄ የያዘው ፖርታል ወደ አፄ ዮሐንስ ለመቅረብ በራስ አሉላ በኩል ማለፍ ነበረበት። በመኾኑም ከምፅዋ በቀጥታ ያመራው የዶጋሊው ባለ ታሪክ ራስ አሉላ ወደሚገኙበት አስመራ ነበር።

ራስ አሉላ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ የጀግንነት ቦታ ካላቸው ጥቂት አርበኞች አንዱ ነው። አሉላ ቀጭን፣ ለግላጋ ወጣት ሲሆን ጎድጓዳ ዐይኖቹ እና ክብ ፊቱ የተለየ ውበት ይፈጥሩለታል። ከፖርታል ጋር የተገናኘበት ወቅት ከሐር የተሠራ ሸሚዝ እና ሱሪ የለበሰ ሲሆን ከበላዩ ደግሞ የአንበሳ ቆዳ ደርቦ ነበር። በቀኝ ትከሻው ጠመንጃ የታጠቀ ሲሆን በብር ያጌጠ ጋሻ ደግሞ በግራ እጁ ይዞ ነበር።



The young Alula. From Lincoln de Castro, *Nella terra dei negus, pagine raccolte in Abissinia*. Milan: Fratelli Treves, 1915.

*ራስ አሉላ*

ራስ አሉላን በቅርብ ከሚያውቁት መካከል የእንግሊዝ መልዕክተኛ የነበረው አጉስተስ ዋይልድ አንዱ ነበር። ዋይልድ ለአሉላ ከፍተኛ ክብር የነበረው ሲሆን የአሉላን ተክለ ሰውነት እና ባሕርይ እንዲህ ነበር የገለጸው፡- *‹‹ራስ አሉላ በአጠቃላይ ጠይም እንግሊዛዊ ይመስላል። መልከመልካም ወጣት ሲሆን የሚያማምሩ ዐይኖች እና ሰልካካ አፍንጫ የታደለ ነው። እንደበተ-ርቱዕ ከመኾኑም በላይ በእሱልነት ያምናል። ለዚህ ማሳያም በዙሪያው የነበሩ አማካሪዎቹ ሙስሊም እና ክርስቲያን መሆናቸውን መመልከቱ በቂ ነበር።››* የኹለቱ መልካም ወዳጅነት የዘለቀው ራስ አሉላ ከአድዋ ጦርነት በኋላ ባልተጠበቀ ሁኔታ እስከሞተበት ዕለት ድረስ ነበር።

ፖርታልን በአስመራ የተቀበለው ራስ አሉላ ዋይልድ ከገለጸው ፈጽሞ የተለየ ነበር። ከሄዊት ስምምነት በኋላ እንደ አፄ ዮሐንስ አሉላም በእንግሊዞች ከሃዲነት ተበሳጭቶ ነበር። በመኾኑም ፖርታል የጣሊያንን ጥቅም ለማስጠበቅ የተላከ መኾኑን የተረዳው ራስ አሉላ አስተያየቱ በጥርጣሬ የተሞላ ነበር። አስመራ የነበረው የራስ አሉላ ጽ/ቤት የተለየ ግርማ ሞገስ ነበረው። በሳር የተከደነው የቤቱ ጣሪያ መሃል ላይ





መስቀል ይታያል። ከመስቀሉ አናት ላይ የተቀመጠው ክብ ቅርፅ ባለቤቱን ከቡዳ እንደሚከላከል ይታመን ነበር።

ፖርታል ወደ ራስ አሉላ እልፍኝ ሲገባ ውስጡ ጨለምለም ያለ በመኾኑ ለሰከንዶች ያህል ዐይኑን ለማላመድ ቆመ። ከእልፍኙ ጥግ ላይ በቀይ ወንበር ላይ የተቀመጠውን ራስ አሉላ እና በርካታ አጃቢዎቹን የተመለከተው ፖርታል በአድናቆት አፉን ከፍቶ ነበር። የወቅቱን ሁኔታሙሉ በሙሉ የጻፈው ፖርታል ራስ አሉላን በተለየ ሁኔታ ነበር የገለጸው። *"የቆዳ ቀለሙ ከበርካታ የትግራይ አካባቢ ወንዶች አንፃር ሲታይ ጠቆር ያለ ሲሆን ብሩህ ዐይኖቹ እና ነጫጭ ጥርሶቹ ከርቀት ይታያሉ። የራስ አሉላ ዓይነት ዐይኖችን ከዚህ በፊት የተመለከትኩት ነብር እና አቦ ሸማኔ ላይ ብቻ ነበር። በሰው ፊት ላይ እነዚያን ዓይኖች ዐያለሁ ብዬ አልጠበቅሁም ነበር።"* በማለት ፖርታል የራስ አሉላን የተለዩ ዐይኖች ገልጿቸዋል።

ፖርታል ከአሉላ ጋር ለመገናኘት ሲያመራ ያማረ የዲፕሎማት ሙሉ ልብስ ነበር የለበሰው። ራስ አሉላ በበኩሉ ሐምራዊ የሃር ሸሚዝ የለበሰ ሲሆን ከአጠገቡ የነበረው ጠረጴዛ ላይ የማርቲኒ-ሄንሪ ጠመንጃው ተደግፏል። የእልፍኙ ግድግዳ በተለያዩ የአራዊት ቀንድ እና ቆዳ አጊጧል። በተሰቀሉት የአራዊት ቀንዶች ላይ የተለያየ ሞዴል ያላቸው ጠመንጃዎች ተንጠልጥለው ይታያሉ።

ፖርታል ውይይቱን የጀመረው ለአሉላ ስጦታ በማቅረብ ነበር። ስጦታውም በዘመናዊነቱ አሉላ ከታጠቀው ማርቲኒ-ሄንሪ ጠመንጃ የተሻለ የሆነው ዊንቼስተር ጠመንጃ ከ500 ጥይት ጋር ነበር። ስጦታው በአሉላ ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ አለማምጣቱን ቅጭም ካለ ገጽታው ላይ መረዳት ይቻል ነበር።

የፖርታል ዋና ተልዕኮ ከአፄ ዮሐንስ ጋር በመገናኘት የሰላም ድርድር ማድረግ የነበረ ቢሆንም ጣሊያን ለዶጋሊው ውሉ ዕውቅና እስካልሰጠች ድረስ እንደማይደራደር አሉላ አሳወቀው። ጣሊያን የጠየቀችውን የጦር ጉዳት ካሳ



The young Alula. From Lincoln de Castro, *Nella terra dei negus, pagine raccolte in Abissinia*. Milan: Fratelli Treves, 1915.

በተመለከተም አሉላ ለፖርታል የገለጹለት እንዲህ በማለት ነበር፡- *«ጣሊያን ለአቲ... መውሰድ የምትችለው እኔን የርም ገዢ ለማድረግ ከተስማማች ብቻ ነው።»* ፖርታል ከአፄ ዮሐንስ ጋር እንዳይገናኝ የፈለገው አሉላ መልዕክተኛውን ለዐሥር ቀናት ያህል የቁም እሥረኛ አድርጎ አስቀመጠው።

ፖርታልን እንዲያስገባው የሚያዝ መልዕክት ለአሉላ ደረሰው። ንጉሡ ጦራቸውን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ በሚያዘምቱበት ወርኃ ነሐሴ አሸንጌ ሐይቅ አቅራቢያ ፖርታል እንዲያገኛቸውም አሉላ አመቻቸ። ፖርታል እና ባልደረቦቹ የንጉሡ ጦር ሲያልፍ ከመንገድ ዳር እንዲመለከቱ ታስቦበት እንደነበር ያለውን ግምት በማስቀደም በወቅቱ የተመለከተውን ወታደራዊ ሰልፍ ፖርታል የገለጸው እንደሚከተለው ነበር።

> *«እኔና ጓደኞቼ ቢቻ በዕለቱ የተመለከትነው የወታደር ብዛት በጥንቃቄ ነበር ያሰላነው። በአንድ ደቂቃ ውስጥ ያለፉትን ወታደሮች በመቁጠር ጀምረን አጠቃላይ ሠራዊቱ ለማለፍ የወሰደበትን ሰዓት ያዝን። በዚህ መሠረት በማስላት የወታደሩ ቁጥር ከ70 ሺህ እስከ 80 ሺህ እንደሚደርስ ገመትን። ከሠራዊቱ መካከል ባማረ በቅሎው ላይ ሆኖ ነበር ንጉሡን የተመለከትነው። ባለቀይ ጥለት ነጭ የአበሻ ሸማ የለበሰ ሲሆን ፊቱም በከፊል ተሸፍኗል። የንጉሡ ቀይ የሐር ጃንጥላ ከተራው ወታደር የተለየ ምልክት ሰጥቷቸዋል።*

ፖርታል አፄ ዮሐንስንም ሆነ የኢትዮጵያን ሙሉ የጦር አሰላለፍ ሲመለከት የመጀመሪያው ነበር። ንጉሡ ለውጊያ ዝግጁ መሆናቸውንም ያረጋገጠው ሰልፉን በመመልከት ነበር።





ፖርታል ከንጉሡ ጋር በተገናኘበት ወቅት ያመጣላቸውን የዊንቼስተር ጠመንጃ እና የጦር ሜዳ መነጽር በስጦታ መልክ አቀረበ። አፄ ዮሐንስም በምላሹ ሙሉ የኢትዮጵያ ልብስ፣ የአንበሳ ለምድ፣ ጦር እና ጋሻ አበረከቱለት። ልብሱን በጣም ስለወደደውም ወደ ካይሮ ሲመለስ በቀጥታ ያመራው ወደ ፎቶ ግራፍ ባለሙያ ነበር።

ድርድሩ ፖርታል እንደጠበቀው አልነበረም። አፄ ዮሐንስ ከአሉላ በላይ የከረረ አቋም ይዘው ነበር የጠበቁት። በድርድሩ ወቅትም *«ሉዐላዊ ክብሬ የተጣሰው እኔ ሆኜ ሳለሁ ለምን ጣሊያን ልትቀጣኝ ትዝታለች?»* በማለት ነበር አፄ ዮሐንስ እምቢታቸውን ለፖርታል የገለጹለት። ድርድሩ ያልተሳካለት ፖርታል በነሐሴ ወር ወደ ምፅዋ ተመለሰ። በተመሳሳይ ወቅት አፄ ዮሐንስ ጦራቸውን በደብልጥ ወደ ሰሜን በማስጠጋት በምፅዋ እና አስመራ መካከል የምትገኘው ጊንዳ ላይ መሸጉ። የጣሊያን ምሽግ ከነበረበት ስእቲ የነበራቸው ርቀትም በጣም ጠበበ።

አፄ ዮሐንስ ጣሊያንን ለመውጋት በተዘጋጁበት ወቅት የማሃዲ ጦር ምዕራባዊ ግዛታቸውን እንደወረረ ሰሙ። ወራሪው ኃይል ጥር 21 ቀን 1888 የጎጃሙን ንጉሥ ተ/ኃይማኖት ድል በመንሳት ወደ ጎንደር አልፎ በከተማዋ ላይ ከፍተኛ ውድመት አደረሰ። ወራሪው ኃይል በርካታ አብያተ-ክርስቲያናት ጨምሮ ቤቶችን በቃጠሎ አወደመ።

አፄ ዮሐንስ ጦራቸውን ወደ ጎንደር ለማዝመት ሲወስኑ ራስ አሉላ በቅድሚያ ጣሊያንን መምታት እንደሚሻል ሀሳብ አቀረበ። ንጉሡ የአሉላን ሀሳብ ሳይቀበሉ መላው ጦራቸውን እንዲሁም ራስ አሉላን አስከትለው ወደመጡበት ተመለሱ። በሚያዝያ 1888 ስእቲ ብቻ ሳይሆን አስመራም ያለ በቂ የመከላከያ ሠራዊት ጥበቃ ሆነው ቀጣይ እጣቸውን በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።

ጣሊያን በዮሐንስ ላይ ተጨማሪ ጫና ለማሳደር መንቀሳቀስ የጀመረችው ቀድሞ ነበር። ራስ አሉላ በአስመራ ጄራልድ ፖርታልን ተቀብሉ ባናገረበት ወቅት የጣሊያን ተወካዮች ደግሞ በአዲስ አበባ የምኒልክን አጋርነት ለማግኘት በመደራደር

ላይ ነበሩ። በዮሐንስ ላይ እንዲነሳ ለማሳመን ጣሊያን ለምኒልክ የጦር መሣሪያ ስጦታ እና የልዩ ወዳጅነት ጥሪ አቀረበችለት። ምክንያታቸው የተለያየ ቢሆንም ጣሊያን እና ምኒልክ የአፄ ዮሐንስ መዳከምና መውደቅ ላይ ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው።

ንግሥናቸው በሸዋ ግዛት ብቻ የተወሰነው ምኒልክ አፄ ዮሐንስን በማስወገድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የመሆን ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። ፍላጎታቸውን በፍጥነት ለማሳካትም የአፄ ዮሐንስን ሞት ጨምሮ የትኛውንም መንገድ ለመጠቀም ዝግጁ ነበሩ።

አፄ ዮሐንስ በበኩላቸው የምኒልክን ዳተኝነት ጠንቅቀው ያውቃሉ። ምኒልክን ለማስገዛትም በ1870ዎቹ ጦራቸውን መላክ ግድ ብሏቸው ነበር። ንጉሠ-ነገሥትነታቸውን በጉልበት የተቀበለው ምኒልክ በየትኛውም አጋጣሚ ዙፋናቸውን ለመነቅነቅ እንደሚሞክር የሚያውቁት ዮሐንስ፣ ጣሊያንን ለመግጠም ወደ ሰሜን ባቀኑበት ወቅት ምኒልክን ያለ በቂ ተከታታይ ትተው መምጣታቸው አሳስቧቸው ነበር። የምኒልክን የዘውድ ጥማት የተመለከተችው ጣሊያን ደግሞ ፍላጎቷን ከምኒልክ ጋር በማቀራረብ አፄ ዮሐንስ ላይ በጋራ ለመነሳት ተዘጋጀች። በመኾኑም ለምኒልክ የንጉሰ ንጉሥትነት ጉዞ አጋዥ በመሆን ለመሰለፍ ወሰነች።

ስለ ኢትዮጵያ በተለየ የአድናቆት ስሜት ተሞልቶ ይናገር የነበረው አጉስተስ ዋይልድ በአንድ ወቅት ስለ ምኒልክ የሚከተለውን ፅፎ ነበር። ‹‹ምኒልክ በከፍተኛ ጉጉት የተሞላ ሲሆን ዮሐንስን ከማስወገድ የሚገታው ነገር ያለ አይመስልም።›› የዋይልድ ገለጻ በአብዛኛው እውነት ቢሆንም በወቅቱ ግልጽ ያልነበረው ምኒልክ በጣሊያኖች ገንዘብ ተደልሉ ዮሐንስን ለመጣል መነሳቱ ነበር። በወቅቱ የምኒልክን ትክክለኛ ፍላጎት ጣሊያኖች በቀላሉ ሊገነዘቡት አልቻሉም ነበር።

በደቡብ በምኒልክ የማይጨበጥ አቋም እንዲሁም በሰሜን በጣሊያን የወረራ ስጋት የተወጠሩት አፄ ዮሐንስ ጦራቸውን በቀጥታ ያዘመቱት በምዕራብ የአገሪቱ





ክፍል ወረራ በፈጸመባቸው የመሃዲስት ጦር ላይ ነበር። አጉስተስ ዋይልድ በምኒልክ አካሄድ ላይ የነበረውን ጥርጣሬ ከጊዜ በኋላ ነበር የጻፈው። እንደ ዋይልድ ከሆነ "ምኒልክ አፄ ዮሐንስን ለመጣል በምስጢር ከመሃዲስት ወራሪዎች ጋር ሳይስማሙ አልቀሩም" በማለት የሸዋው ንጉሥ አገር የመክዳት ድርጊት እንደፈጸሙ ጽፏል።

በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ የዮሐንስ ሠራዊት ብልጫውን ይዞ ነበር። ከአፍታ በኋላ አፄ ዮሐንስ ከመሃዲስት በተተኮሰ ጥይት ሲቆስሉ ጦራቸው በመሃዲስት መበለጥ ጀመረ። በርካታ የኢትዮጵያ ሠራዊት የቆሰሉ ንጉሣቸውን በመከበብ የመከላከል ውጊያ እያደረጉ ማፈግፈግ ጀመሩ። በኹለተኛው የውጊያው ዕለት ውሎ የመሃዲስት ጦር የኢትዮጵያን ሠራዊት በመውረር የአፄ ዮሐንስን ራሳ ማርኮ ጭንቅላታቸውን ቆርጦ ወሰደ። ለአንፀባራቂ ድላቸው ማረጋገጫም የንጉሡን ጭንቅላት ለቀናት ያህል በካርቱም አደባባይ ለዕይታ አስቀምጠውት ነበር።

የዮሐንስን ዘውድ ማን ይረከበዋል? በሞት አፋፍ ላይ ሳሉ አፄ ዮሐንስ ልጃቸው መንገሻ የዘውዳቸው ወራሽ እንዲሆን ተናዘው እንደነበር ይነገራል። የሟቹ ኑዛዜም መንገሻ ለዘውዱ እንዲንቀሳቀስ መንገድ ከፍቶለታል። የአባቱን ዘውድ ለመውረስ ግን ከፍተኛ የሆነ ተግዳሮት ከፊቱ ይጠብቀዋል።

# ምዕራፍ አራት

# የነጻነት ዋጋ

አዲስ አበባ ከዘመቻ በመመለስ ላይ የነበሩትን ባለድል ንጉሥ ምኒልክ ለመቀበል ሽርጉድ እያለች ነበር። በወላይታ ሕዝብ እና ንጉሥ ላይ ጥር 18 ቀን 1895 ድልን የተቀዳጁት ምኒልክ ከአንድ ቀን በኋላ አዲስ አበባ ሲደርሱ ደማቅ አቀባበል ይጠብቃቸዋል። ንጉሡ አዲስ አበባ መግቢያ ላይ የደረሱት በጥቅምት ዋዜማ በከተራ በዓል ስለነበር ምሽቱን በከተማ ዳርቻ በማሳለፍ በዕለተ ጥቅምት ወደ መሃል ለመግባት ወሰኑ። በጥምቀት ዋዜማ ለዚያውም በዓም ዕለት አዲስ አበባ በመግባት ድላቸውን ለሕዝብ ያሳበሰሩት በሕዝቡ ዘንድ በዓም ቀን ድልን ማብሰር የመጥፎ ዕድል አመላካች መኾኑ ስለሚታመን ነበር። በመኾኑም ንጉሡ በዕለተ ጥምቀት ለመግባት የከተራ በዓልን ከከተማዋ ውጪ አሳለፉ።

በማግስቱ ደማቁ የንጉሡ የአገባብ ሥርዓት የተጀመረው በካህናት ሰልፍ ነበር። በባለድባብ ጃንጥላ እና የቀሳውስት አልባሳት የደመቀው ሰልፍ ታቦታትን በማጀብ በዝግታ አለፈ። ከድል የተመለሰው ሠራዊት ካህናት እና ቀሳውስቱን ተከትሎ ተመመ። ቁጥራቸው ወደ ሠላሳ የሚጠጉ ባለ ነጋሪት፣ አታሞ እና እምቢልታ ሰልፈኞች ከፊት ሆነው ለፈረሰኛ ወታደሮች መንገድ እየመሩ አለፉ።

በበርካታ የጦር መሪዎቻቸው የታጀቡት ምኒልክ ከሰልፈኛ ሠራዊቱ መካከል ታጅበው በዝግታ ይራመዳሉ። አፈ ንጉሣቸው ከፊት ሆኖ ሲመራቸው ከጀርባቸው ደግሞ በርካቶች ጥሩንባ እየነፉ ተከተሏቸው። የሙገሳ ቀረርቶ እና ሽለላዎችን ተከትሎ «የእንኳን ደኅና መጡ» ተኩስ ተደረገ። በመቀጠል ከኅዳር ወር ጀምሮ ባሎቻቸው፣ ልጆቻቸው እና ወንድሞቻቸው ዘመቻ ቀይተው የተመለሱላቸው ሴቶች በከፍተኛ ድምፅ እልልታቸውን አሰሙ።





የድል መልስ ፌሽታው እንደ ጥንታዊ ሮማውያን ሥነ-ሥርዓት እርስ በእርስ በመሞጋገስ ላይ የተመሠረተ ነበር። ባለድል ነገሥታት በወታደሮቻቸው ይሞገሳሉ፣ ይወደሳሉ። ሕዝቡም ባለድል ሠራዊታቸውን በከፍተኛ ድምፅ እየጮኸ ይቀበላቸዋል።

የወታደሮች እና የምርኮዎች ሰልፉ በአጠቃላይ ሦስት ቀናት የፈጀ ነበር። የወላይታ የኢኮኖሚ መሠረት እርሻ እና ከብት እርባታ ላይ የተመሠረተ በመኾኑ የምኒልክ ሠራዊት እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ከብት ይዞ ነበር የተመለሰው። በተጨማሪም ወደ ዐሥራ አምስት ሺህ የሚደርስ የወላይታ ሠራዊትም በምርኮ ተይዞ መጥቷል። ምርኮኞች በባርነት ከማገልገል የተለየ ዕድል አይጠብቃቸውም። በዘመቻው ለተሳተፉ የምኒልክ ወታደሮች በሽልማት መልክ እስኪከፋፈሉ ድረስ በግዞት ይቆያሉ።

የሰልፉ ከፍተኛ ድምቀት የነበረው የምርኮኛው የወላይታው ንጉሥ ጦና ያለፈበት ነበር። የምኒልክን ወረራ ለመከላከል ሕዝቡን በጥሩ ሁኔታ አደራጅቶ የተዋጋ ቢሆንም አልተሳካለትም ነበር። የምርኮኛው ንጉሥ ጦና በሰልፉ መኖር የምኒልክን ድል ምሉዕነት አስመስክሮ ነበር። የጦና በምርኮ መያዝ በወላይታ ሕዝብ ዘንድ የነበረውን ክብሬታ በማሳጣት ሕዝቡ ምኒልክን እንዲያከብር ያደርጋል። ምርኮኛውን ለሕዝቡ ማሳየት ያለውን ፖለቲካዊ ትርፍ ምኒልክ ቀድመው ስለተረዱ ነበር ቁስለኛውን ንጉሥ ጦና አክመው የሰልፉ አካል ያደረጉት።

የጦና የፍርድ ሂደት የተጀመረው ከቀናት በኋላ ነበር። ንጉሥ ጦና ክርስትናን ለመቀበል ከተስማማ በኋላ ምኒልክ ይቅርታ አደረጉለት። ከይቅርታው በኋላም ነጭ የሐር ልብስ እና ጥቁር የንጉሥ ካባ በአግባቡ አልብሰው ፎቶ ግራፍ አሥነስተውታል። በወቅቱ ከምኒልክ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነጭ ሻሽ በራሱ ላይ ተጠምጥሞ ዘውድም ተጫነለት። ንጉሥ ጦና ፎቶግራፍ በተነሳበት ወቅት ፊቱ ላይ የሚታየውን ስሜት ለመግለጽ ያስቸግራል።

ንግሥናውን በማጽደቅ ምኒልክ ጦናን ወደ ወላይታ ገዢነቱ ለመመለስ የወሰኑት ንጉሡ ሕዝቡን እርሳቸው ከሚልኳቸው እንደራሴዎች የተሻለ ስለሚያውቅ ነበር፡፡ ሽንፈቱን በጸጋ በመቀበሉም ምንም ዓይነት የማፈንገጥ ሙከራ እንደማያደርግ ገምተው ነበር፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የወላይታ ሕዝብ በምርታማነቱ ይታወቃል፡፡ በመኾኑም ጦናን ወደ ግዛቱ በመመለስ ዓመታዊ ግብርን በአግባቡ በመሰብሰብ እንዲልክላቸው ነበር ምኒልክ ያሰቡት፡፡

የወላይታው ዘመቻ ለምኒልክ ወታደራዊ ድል እና ኢኮኖሚያዊ ጉልበትን ቢፈጥርላቸውም በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ቁጣን ቀስቅሰባቸዋል፡፡ አውሮፓውያን አፍሪካ ውስጥ ለሚደረግ የእርስ በእርስ ጦርነት ግድ እንደሌላቸው ያሰቡት ምኒልክ ስሕተታቸውን የተረዱት ዘግይተው ነበር፡፡ የፈረንሳይ መልዕክተኛ የነበረው ጂን ጋስተን ቫንደርሄይም ወደ አውሮፓ ሲመለስ ስለምኒልክ ውስጣዊ ዘመቻ በማጋለጥ የንጉሡ ድርጊት እንዲወገዝ አደረገ፡፡

ምኒልክ ቫንደርሄይምን ማመን አልነበረባቸውም፡፡ ለፈረንሳይ ነጋዴዎች ገበያ ለማፈላለግ በ1884 ክረምት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ቫንደርሄይም የምኒልክን አመኔታ ለማግኘት ብዙ ጊዜ አላስፈለገውም፡፡ የዘመቻ ስኬታቸውን እንዲመሰክት እና ለአውሮፓ ምስክርነቱን እንዲሰጥላቸው በማሰብ ነበር ምኒልክ ዐሥራ ኹለት አጃቢ መድበውለት ወደ ወላይታ የወሰዱት፡፡ ቫንደርሄይም አጋጣሚውን በመጠቀም የጋዜጠኝነት ሥራውን ተያያዘው፡፡ ቫንደርሄይም ፈረንሳዊው ፓውል ናዳር በሠራው የፎቶ ካሜራ በመታገዝ የወላይታውን ዘመቻ ሙሉ ታሪክ ለመያዝ ቻለ፡፡

ምኒልክ ወደ ወላይታ ያደረጉትን ዘመቻ እንደ ክርስቲያናዊ ቅዱስ ተግባር ነበር የተመለከቱት፡፡ የወላይታ ሕዝብ ቀድሞ ክርስቲያን እንደነበሩ እና በ17ኛው ክፍለዘመን በአህመድ ኢብን ኢብራሃም አል-ጋዚ ዘመቻ አማካይነት ወደ እስልምና እንደተቀየሩ የሚያምኑት ምኒልክ በዘመቻቸው የወላይታን ሕዝብ ከእስልምና ጭቆና





ነፃ እንደሚያወጡ በማሰብ ነበር ዘመቻቸውን ያካሄዱት፡፡ የወላይታ ሕዝብ መፃኢ ዕድል በተለይም ከምኒልክ ወረራ በኋላ የኃይማኖት ለውጥ ግዴታ ነበር የሆነው፡፡

ጦና የምኒልክን ጦር ኃያልነት መቋቋም አልቻለም፡፡ ምኒልክ ዘመቻቸውን ባወጁበት ወቅት ቁጥሩ ከ80 ሺህ በላይ የነበረው ሠራዊታቸው በምሥራቅ አፍሪካ እጅግ ግዙፍ መኾኑን ያስመሰከረ ነበር፡፡ በአፄ ዮሐንስ ሞት ዋዜማ የምኒልክ ጦር በቁጥሩም ሆነ በይዘቱ የዮሐንስን ጦር በልጦ ነበር፡፡ ለጣሊያን፣ ፈረንሳይ እና ለግለሰብ የጦር መሣሪያ ነጋዴዎች ምስጋና ይግባቸው እና የምኒልክ ሠራዊት ዘመናዊ የጦር መሣሪያም ታጥቆ ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር ሲገመገም የወላይታ ጦር ከምኒልክ ሠራዊት ፊት መቆም የማይችል ነበር፡፡

የምኒልክ ጦር መንቀሳቀስ ሲጀምር እቴጌ ጣይቱ ብጡል በወላይታ ላይ ሊደርስ የሚችለውን እስፈሪ እልቂት በመገመት ምኒልክን እና የጦር አዝማቾቻቸውን ሳይቀር ተማፅነው ነበር፡፡ በዚህ ውጥረት መካከል ንግሥቲቷ ታመው አልጋ ሲይዙ ምኒልክ አጋጣሚውን ተጠቅመው ዘመቻውን አዘዙ፡፡ በጥቂት ቀናት እንደሚመለሱም ለንግሥቲቷ ተናግረው ነበር፡፡

## ምኒልክ ወደ ወላይታ ያደረጉት ዘመቻ

ምኒልክ ለዘመቻ የመረጡት የክረምቱ ማለቂያ የሆነው ወርኃ ኅዳር ነበር፡፡ የአጠቃላይ ዘመቻው መሪ አድርገው የሾሙት የራስ ሚካኤልን ጦር ነበር፡፡ ምኒልክ ከእስልምና ወደ ክርስትና የተቀየሩትን ራስ ሚካኤል በመሪነት ሲመርጡ አንድም የራስ ሚካኤልን ታማኝነት ለመፈተሽ በሌላ በኩል ደግሞ የሙስሊሙ የወላይታ ሕዝብ ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ከራስ ሚካኤል ተመሳሳይ መኾኑን ለማመላከት ነበር፡፡ በራስ ሚካኤል ሰባት ሺህ ሠራዊት ፊት አውራሪነት ከዐሥራ ሦስት ሺህ እስከ ዐሥራ ስምንት ሺህ የሚደርስ ቁጥር ያለው የምኒልክ ጦር የጦናን ሠራዊት ለማፍረክረክ ተንቀሳቀሰ፡፡

የዘመቻ እንቅስቃሴው በአጠቃላይ ሲታይ የሚንቀሳቀስ የጦር የጎራዴ እና የድንኳን ጫካ ነበር የሚመስለው። እያንዳንዱ ራስ እና አዝማች የየራሱን አጃቢ እና ወታደር አስከትሎ ነበር የሚንቀሳቀሰው። በአሰላለፋቸውም የምኒልክ ጦር የራሶችን እና የአዝማቾችን ጦር እንደየተዋረዳቸው እና ማዕረጋቸው አስከትሎ ነበር የሚጓዘው። ስንቅ እና ትጥቅ ከተጫኑት የጋማ ከብቶች በተጨማሪ ማር፣ ቅቤ እና በርበሬ ያዘሉ ሴቶችም አብረው ዘምተዋል።

ምኒልክ ለንግሥት ጣይቱ ብጡል ቃል የገቡት ዘመቻው በአጭር ጊዜ እንደሚጠናቀቅ ቢሆንም እስከ ታኅሳስ ወር መጨረሻ ድረስ የዘመቻው ዜና አዲስ አበባ አልደረሰም ነበር። ዘመቻው ከተገመተለት ጊዜ በላይ እንዲወስድ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ምኒልክ የወላይታን ጦር አሳንሰው መገመታቸው ነበር። የወላይታ ሕዝብ በቀይ ለም መሬት ላይ የተመሠረተ የግብርና ህይወቱ ሀብታም ያደረገው ሲሆን ከግብርናው በተለየ ግን ጠንካራ ተዋጊ መኾኑ ለወራሪው የምኒልክ ጦር አዳጋች ሆኖበት ነበር።

የወላይታ አመራር በውጊያው ወቅት ያሳየው ብቃት የሚደነቅ ነበር። ንጉሥ ጦና እየመጣበት የነበረውን ግዙፍ ጦር ለመግጠም የመረጠው ስልት የሽምቅ ውጊያን ነበር። ጦራቸው የወላይታ ግዛት እንደደረሰ ምኒልክ ንጉሥ ጦና እጁን ይሰጥ ዘንድ እንዲህ ሲሉ ጠየቁት። «ሕዝብህን አታስፈጅ፤ ግዛትህንም አትጣ። እጅ ስጥ። ግብርንም ክፈል።» በወቅቱ የነበሩ የምኒልክ ጸሐፍት የንጉሥ ጦና ምላሽ እንዲህ እንደነበር ጠቅሰዋል።

«ክርስቲያኖች ወደ ግዛቴ እንዲገቡ አልፈቅድም፤ ለእነርሱም አልገብርም። ለመፋለም ዝግጁ ነኝ።»

የንጉሥ ጦና ሠራዊት የመከላከል እርምጃ የጀመረው ገና የምኒልክ ጦር በመንገድ ላይ ሳለ ነበር። ጉድጓድ በመቆፈር እና ወጥመድ በማጥመድ ቀድሞ





የተዘጋጀው የጦና ሠራዊት በርካታ የምኒልክ ወታደሮች እና የጋማ ከብቶች ላይ ጉዳት አደረሰ። በተጨማሪም የምኒልክ ሠራዊት ቁጥቋጦ በመመንጠር እንዲሁም መንገድ በማስተካከል ስለተጠመደ ነበር ዘመቻው ተጨማሪ ቀናትን የወሰደው።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ወላይታ መዲና ሲቃረብ የጦና ሠራዊት በማፈግፈጉ ሽንፈቱን ማዘግየት ቻለ። ያም ሆኖ ግን ንጉሥ ጦና የወላይታን ሕዝብ ያለምንም ተከላካይ ለምኒልክ ሠራዊት ጥሎ ነበር የሸሸው። የጦናን የሽምቅ ውጊያ ደግፈዋል በሚል ሰበብ የምኒልክ ሠራዊት በተራው ሕዝብ ላይ እርምጃ መውሰድ ጀመረ። ራስ ሚካኤልም ሠራዊታቸውን በማዝመት በርካታ የወላይታ መኖሪያ ቤቶችን እና የንብ ቀፎዎችን በእሳት አወደሙ።

የበርካታ መንደር ነዋሪዎች ለምኒልክ ሠራዊት እጃቸውን ሰጡ። አንዳንዶች ደግሞ የምኒልክን ሠራዊት መንደራቸው ከመድረሱ አስቀድሞ ለሠራዊቱ የዛፍ ቅርንጫፍ በማሳየት ተንበረከኩ። ምርኮኞችም በፈቃዳቸው ለምኒልክ ለመሰለል እና ጦና የመሸገበትን ቦታ ለመጠቆም ተስማሙ።

ንጉሥ ጦና የመሸገበት ቦታ እንደታወቀ የምኒልክ ሠራዊት ስንቅ እና ትጥቅ አቅራቢዎችን ወደ ኋላ በመተው በምሽት ዘመተ። እስከ አባያ ሐይቅ ድረስ በመዝመትም የጦናን ይዞታ በምዕራብ እና በምሥራቅ አቅጣጫ በመክበብ መውጪያ አሳጡት። ከበባው እየጠበበ መኾኑን የተመለከተው ንጉሥ ጦና የማምለጥ ሙከራ ቢያደርግ ራሱን እንደሚያጠፋ ገባው። ቀጣዩ ሥራ የምኒልክ ግዙፍ ሠራዊት እና የጦር መሣሪያው ነበር።

ታኅሳስ 11 ቀን የጦና ሠራዊት ባልቻ በሚመራው የመድፈኛ ብርጌድ ተከበበ። በሰላሙ ቀን የምኒልክ ግምጃ ቤት ኃላፊ በመሆን የሚያገለግሉት ባልቻ በጦርነቱ ወቅት የመድፈኛው ጦር መሪ በመሆን አገልግለዋል። የባልቻ ሠራዊት የሚተኩሳቸው ጥይቶች በጦና ሠራዊት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከተሉ። በከባ ቅጠል

ተሸፍነው የነበሩት የጦና ወታደሮች ቀስት ለመወርወር ብቅ ሲሉ የተቀበላቸው የባልቻ ሠራዊት ጥይት ነበር።

ንጉሥ ጦና ታኅሳስ 13 ቀን በቁጥጥር ሥር ቢውልም ጦርነቱ ግን ለቀናት ቀጥሎ ነበር። ታኅሳስ 18 ቀን የመጨረሻው ዘመቻ ተጠናቀቀ። ንጉሥ ጦናም በምኒልክ ፊት ቀርቦ የሚከተለውን የፀፀት ንግግር አደረገ።

*«የእራሴን ክብር ማስቀደሜ ስሕተት ነበር፤ አገሬ እንዲህ ወድሞ እና ሕዝቤም ተጨፍጭፎ ከምመለከት ለአንተ እጄን ብሰጥ ይሻል ነበር። የሕዝቦቼ ሞት ለእኔ ይሁን።»*

ንጉሥ ጦና ለሕዝቡ ማለቅ ራሱን ተጠያቂ በማድረግ ይናዘዝ እንጂ በወላይታ የተደረገው ግድያ እና ዘረፋ ቀድሞ በሐረር እና በከፋ ዘመቻ የተሳተፉትን የምኒልክ ሠራዊት አባላት ሳይቀር ያስደነገጠ ነበር። በርካታ አጋሮቻቸውን በጦና የሽምቅ ውጊያ ያጡት የራስ ሚካኤል ሠራዊት አባላት በበቀል ስሜት ተገፋፍተው ብዙ ቁጥር ያለው የወላይታ ሕዝብ ገደሉ። ግድያውን ያቆሙት ከምኒልክ ቀጥታ ትዕዛዝ ከደረሳቸው በኋላ ነበር።

ወራሪው ጦር በምርኮ ለያዛቸው የወላይታ ተወላጆችም ርኅራኄ አላሳየም ነበር። ዘመቻው የዐይን ምስክር የነበሩ የታሪክ ጸሐፍት ጭፍጨፋውን የገለጹት እንዲህ በማለት ነበር። «የወላይታ ሕዝብ በአንዲት ጀንበር ነበር የተፈጀው።» ይህ በእርግጥ የተጋነነ ቢሆንም ምኒልክ የሟች እና ምርኮኛ ወላይታዎች ቁጥር እስከ 18 ሺህ እንደሚደርስ ተናግረዋል። የወቅቱ ታሪክ ጸሐፊ የሟቹ ቁጥር 18 ሺ 987 እንደነበር ቢጽፍም ሻንደርሃይም በበኩሉ ቁጥሩ ከዚያ በታች መኾኑን ነበር የገለጸው።

በአውሮፓ እንደሚታወቀው ኹሉ በአፍሪካ የሚደረጉ ጦርነቶች ለባለድሉ በርካታ የሐብት ማጋበሻ አጋጣሚዎች ናቸው። በእርግጥ ሐብቱ የሚገኘው በአጋጣሚ





ሳይሆን ጦርነቱ ራሱ የሚደረገው የሐብት ማግኛ አጋጣሚን ለመፍጠር ነው። የምኒልክ ወታደሮችም በወላይታ ዘመቻ ወቅት በጭነትም ሆነ በሸክም አቅማቸው የፈቀደላቸውን ያህል ዘርፈው ተመልሰዋል። የወቅቱን ዘረፋ ሻንደርሄይም ሲጽፈው ወታደሮቹ ከጎመን ጀምሮ ዶሮ፣ የቀንድ እና የጋማ ከብት ዘርፈዋል። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የወላይታ ተወላጆችም በባርነት ተጋዙ።

በ1888 የተከሰተው የከብት በሽታ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን እና የከብቶቻቸውን ሕይወት እንደቀጠፈ ይታወሳል። በሸዋ አካባቢ እጅግ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ በወረርሽኙ ያለቀ ሲሆን አንዳንዶች የሟቹ ቁጥር ከአጠቃላይ ሕዝቡ ሲሶ ያህል እንደነበር ይናገራሉ። ምኒልክ ወደ ወላይታ ዘምተው ሲመለሱ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የወላይታ ሕዝብ በግዞት ይዘው መመለሳቸው ምናልባትም በወረርሽኙ ያለቀው ሕዝባቸውን ቁጥር ለመመለስ ያለመ ሙከራ ይመስላል።

በዘመቻው ከተገኘው የምርኮ ሐብት ውስጥ ከፍተኛው መጠን ለምኒልክ ነበር የተሰጠው። ከሠላሳ አምስት ሺህ የቁም ከብቶች ግማሹን እንዲሁም በባርነት ከተጋዙት ዐሥራ ስምንት ሺህ ምርከኞች ደግሞ አንድ ዐሥረኛ የሚኾኑት የምኒልክ ድርሻ ነበሩ። ምኒልክ ድርሻቸው የነበሩት አንድ ሺህ ስምንት መቶ ምርከኞች እጅ ላይ የመለያ መስቀል ምልክት በእሳት እንዲነቀሱ አደረጉ። በመልስ ጉዞው ወቅት የምኒልክ ምርኮኞች ከወታደሩ ጋር ተቀላቅለው እንዲጓዙ ተፈቅዶላቸው ነበር።

በመልስ ጉዞው ወቅት ታኅሳስ 29 ቀን የምኒልክ ሠራዊት መንገድ ላይ እረፍት በማድረግ ደማቅ የወታደራዊ ሰልፍ ትርዒት አሳየ። ምኒልክ በተዘጋጀላቸው ማረፊያ ድንኳን ሥር ተቀምጠው ነበር። ምርኮኛው ንጉሥ ጦና እና የጦር አዝማቾቹ ከምኒልክ እግር ሥር ተቀምጠው ወታደራዊ ትርዒቱን ተመለከቱ። በሰልፉ መጀመሪያ ላይ ፈረሰኛ ወታደሮች እግረኞችን አስከትለው በማለፍ ተመሙ። በመጨረሻም የመልስ ጉዞው ከመጀመሩ በፊት ትርዒቱ በተደረገበት ጉብታ ላይ መኖሪያ ቤት

እንዲሠራላቸው በማዘዝ ምኒልክ የአዲሱን ግዛት ወደ ማዕከላዊ አስተዳደራቸው መቀላቀል አወጁ።

## የምኒልክ ዘመቻ በውጪው ዓለም ዕይታ

ዘመቻው ለምኒልክ ያስገኘላቸው ስኬት ወታደራዊ ብቻ አልነበረም። ከውጪ ወራሪ ለመከላከል ያስፈልጋቸው የነበረውን ገንዘብም ከዘመቻው ማግኘት ችለው ነበር። ወራቸው ከጣሊያን ጦር ጋር ከመግጠሙ በፊት ወታደራዊ አቋሙን ለመፈተሽ የቻለበት ተግባራዊ ዘመቻም ነበር - የወላይታው ዘመቻ። በዘመቻው የተገኘው ድል እና ልምድ ለአዲስ ምልምል ወታደሮች ከፍተኛ ልምድ አስገኝቶላቸዋል።

በዘመቻው ምኒልክ ከፈረንሳዊው ነጋዴ ሲዮን ቼፍኔክስ ላይ የገዟቸውን ዐሥራ አምስት ሺህ ግራስ ጠመንጃ ለመሞከር ቻሉ። በርካታ ቁጥር የነበረው ጠመንጃ ስድስት ወይም ሰባት ዙር ከተኮሰ በኋላ ባዶውን ቀለሃ ለማውጣት ባለመቻሉ ከጥቅም ውጪ የሆነበት አጋጣሚ ነበር። በጠመንጃቸው ብልሽት የተነሣም በርካታ የምኒልክ ሠራዊት ጦር እና ጎራዴ በታጠቁት የጦና ወታደሮች እጅ ላይ ጥሏቸው ነበር።

የቫንደርሃይምን የወላይታ ዘመቻ ዘገባ በርካታ የአውሮፓ ጋዜጠኞች በተቀባበሉት ማግስት ጀምሮ ምኒልክ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ገቡ። በአውሮፓውያን ዘንድ በጥበበኝነት እና ሰብዓዊነት ይገለጽ የነበረው የአፍሪካው ክርስቲያን ንጉሥ ምኒልክ ገጽታ ጥቀርሻ ለበሰ። ከጣሊያን ጋር ለመዋጋት በከፍተኛ ሞራላዊ ብቃት ላይ ለነበሩት ምኒልክ የአውሮፓ ጋዜጦች ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረው ነበር። ቫንደርሃይም በዘገባው ምኒልክ እና ወታደሮቻቸው ምርኮኞችን በባርነት መከፋፈላቸውን ማጋለጡን ተከትሎ ምኒልክ በባሪያ ፈንጋይነት ተወቀሱ። ይህንን ተከትሎ የአውሮፓ የባሪያ ንግድ ከልካዩ የጦር ምርኮኞች፣ የቤት ውስጥ ሠራተኞችን እና ሙስሊሞችን እስማጠቃለሉን በመጥቀስ በአውሮፓ ሰፊ ክርክር ተነሳ።





የቫንደርሃይም ዘገባ ስላስከተለው ተቃውሞ ምኒልክ የሰሙት ዘግይተው ነበር። የአጸፋ ዘገባ እንዲጽፍላቸው ከሰሚር ሞንዶን - ቪዳይሌትን አግባቡ። ሞንዶን በሚያዝያ ወር ለ«ሌ ቴምፕልስ» ጋዜጣ በላከው ዘገባ የወላይታውን ዘመቻ ውጤት ከታሪክ እና ከኃይማኖት አግባብ ነበር ያስቀመጠው። የሞንዶን ዘገባ ከሞላ ጎደል ይህንን ይመስል ነበር።

*«የወላይታ አገረ መንግሥት ከብዙ ክፍለዘመናት በፊት የኢትዮጵያ ግዛት አካል የነበረ ነው። የወላይታ ሕዝቦች ለዘመናት የተጫነባቸውን የእስልምና ተፅዕኖ ተቋቁመው ክርስቲያናዊ ባሕላቸውን ጠብቀው ቆይተዋል። የምኒልክ ዘመቻ የግፍ ወረራ ሳይሆን የቀድሞ ግዛትን የማስመለስ እና ክርስትናን የመጠበቅ ቅዱስ ተግባር ነው። መስቀል በጨረቃ ላይ የበላይነቱን ባሳየበት በዚህ ዘመቻ ለዘመናት ከእናት ሀገሩ የተለየው ግዛት ወደ ክርስቲያን አገዛዝ ተመልሷል። ምስጋና ለሬሚንግተን እና ግራስ ጠመንጃዎች ይሁን እና ኃይል ኃይልን ገዝቶታል።*

የምኒልክን ዘመቻ በተመለከተ በመላው አውሮፓ የተነሣው ተቃውሞ አፀፋ ሲጽፍ በኢትዮጵያ እና አውሮፓ መካከል ላለው ክርስቲያናዊ ቁርኝት ትኩረት ሰጥቷል። በአንዱ ጽሑፍም «አፄ ምኒልክ ከአውሮፓውያን የሚጠብቁት እስተያየት በክርስቲያናዊ ፍትሕ እና መረዳዳት ላይ የተመሠረተ ነው።» ብሎ ነበር።

ሞንዶንን ካገኙ በኋላ ምኒልክ ቫንደርሃየምን ፊት ነሱት። ከቤተ መንግሥታቸው በግልጽ የገፉት ቫንደርሃይምም ጓዙን ጠቅልሎ ለጥቂት ሳምንታት እረፍት ለማድረግ በሚል ሰበብ ወደ ሐረር ለመሄድ ተዘጋጀ። ምኒልክ መልካም አሸኛኘት ቢያደርጉለትም ለሃገሩ ገዢ ራስ መኮንን አያይዘው በላኩት ደብዳቤ ቫንደርሃይምን ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት ቀድመው ወጥነው ነበር። በሐረር ስለሚጠብቀው የሽፍጥ አቀባበል እና ሴራ ለቫንደርሃይም የነገሩት በቤተ-መንግሥት የነበሩ ወዳጆቹ ናቸው።

ከታጠቁ አጃቢዎቹ ጋር በመሆን የሐረር ጉዞውን የጀመረው ሻንደርሃይም በመንገድ ላይ ሳለ አስቸኳይ ደብዳቤ መላክ እንዳለበት ለአጃቢዎቹ ተናገረ። በመኾኑም ወደ ራስ መኮንን ከመሄዱ በፊት ወደ ጠረፍ እንዲያደርሱት እጥፍ ክፍያ እንደሚከፍላቸው ቃል በመግባት አጃቢዎቹን አግባባ። ሐረርን ወደ ጎን በመተውም በቀጥታ ወደ ጅቡቲ አመሩ።





# ምዕራፍ አምስት

## የነጭ ቅጥረኛ ጥቁሮች

‹ዶጋሊ›› እና ‹‹አምስት መቶዎቹ›› የሚሉት ቃላት በጣሊያን ሕዝብ ዘንድ ኢ-ፍትሃዊ ተስፋፊነት የሚያስከትለውን ቅጣት የሚያስታውሱ ቃላት ናቸው። በርም የቆመው የአምስት መቶዎች ሰማዕታት ሐውልት የጣሊያን መንግሥት ወደፊት ለሚያደርገው ወረራ ለድጋፍ ማግኛ እንደ መሣሪያ ሊጠቀምበት አሰቧል። ለጣሊያን ጥቅም ለመዋጋት ዝግጁ የኾኑ ቅጥረኛ አፍሪካውያን እያሉ ስለምን የጣሊያን ውድ ልጆች ለጦርነት ይማገዳሉ?

ከዶጋሊ በኋላ ጣሊያን ከአፍሪካ ቅጥረኛ ወታደሮችን ለመመልመል ወሰነች። ግብፅ በ1870ዎቹ ኢትዮጵያን ለመውረር ስትዘጋጅ በርካታ አውሮፓውያን እና አሜሪካውያን ወታደሮችን ቀጥራ ነበር። በአሜሪካ የእርስበእርስ ጦርነት የተሳተፉትን ጨምሮ በ1864ቱ እና በ1866ቱ የአውሮፓውያን ጦርነቶች የተሰማሩ የዴንማርክ፣ ጀርመን እና ኦስትሪያ ወታደሮችን ቀጥራ ነበር። በወቅቱም ቅጥረኛ መኮንኖች የግብፅ ጦርን በመምራት ኢትዮጵያን ወርረው ነበር።

ጣሊያንም በተመሳሳይ በምሥራቅ አፍሪካ የነበራትን የጦር ኃይል ለማጠናከር ከአካባቢው ነዋሪዎች ልዩ የወታደራዊ ቅጥር ጥሪ አቀረበች። የጣሊያን ማስታወቂያ በቀጠናው በስፋት ከተሰራጨ በኋላ በርካታ የቀይ ባሕር ዳርቻ ነዋሪዎችን ጨምሮ የሱዳን ዜጎችን እንዲሁም እስከ ጎንደር እና ሸዋ በመዝለቅ ኢትዮጵያውያን ቅጥረኛ ወታደሮችን መመልመል ቻለች። የዘር፣ የቋንቋ እና የኃይማኖት ልዩነት ባለማድረግም ኹሉን አቀፍ የሆነ ምልመላ በማድረግ ሙስሊም እና ክርስቲያን አባላት ያሉት ምልምል ሠራዊት ገነባች።

ምልምሎችን ሰብስቦ በማሰለፍ የመረጣ ሥራው ይጀመራል። አውሮፓዊ መኮንኖች በሰልፈኞቹ መካከል በመዘዋወር አካላዊ ብቃታቸው እና ዕድሜያቸው ለወታደራዊ ግልጋሎት ብቁ ያልኾኑትን የመለየት ሥራ ይሠራሉ። የተመረጡትን ምልምሎች ርቀቱ እስከ ዐሥር ማይል በሚደርስ ጋራ እና ሸንተረር ላይ በማስሮጥ በፈረስ የሚከታተሏቸው አውሮፓውያን መኮንኖች ምርጫቸውን ይቀጥላሉ። በሩጫው ተጸክመው የሚንጠባጠቡትን በመተው ባለ ጥሩ ትንፋሽ የኾኑትን ጥቂት ምልምሎች ለቀጣይ ሥልጠና ያጫሉ።

ከአካል ብቃት ፈተናው ቀጥሎ የጤና ምርመራ ይደረጋል። ጤነኞች ተለይተው ገላቸውን እንዲታጠቡ ከተደረገ በኋላ ወታደራዊ የደንብ ልብስ ይታደላቸዋል። በምሥራቅ አፍሪካውያን ዘንድ የተለመደ የነበረውን ነጣ ያለ ቁምጣ እና ሸሚዝ ነበር የታደሉት። ቁምጣው ጉልበታቸው አካባቢ ጠባብ ሆኖ ዳሌያቸው አካባቢ ደግሞ ሰፋ ተደርጎ የተሰፋ ነበር።

ወታደራዊው የደንብ ልብስ አብዛኞቹ ምልምሎች ከዚያ በፊት ለብሰውት የማያውቁት ዓይነት ምርጥ ልብስ ነበር። ከቁምጣና ሸሚዙ በተጨማሪ አጭር ኮት እና ቀይ ኮፍያ ተጨምሮላቸው ደመቁ። በመጨረሻም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃ እንዲሁም በቀይ ቆዳ የተሠራ የጥይት ማስቀመጫ ዝናር ታደላቸው።

### የባንዳ ባታሊዮኖችን ማደራጀት


ልዩ የመለያ ቀበቶ የተሰጣቸው አዳዲሶቹ ምልምሎች በተለያዩ ቀጠናዎች ተመደቡ። የመጀመሪያዎቹ አራት ባታሊዮን አባላት አራት የተለያዩ ቀለማት (ቀይ፣ ሰማያዊ፣ ሃምራዊ እና ጥቁር) ቀበቶዎችን ያጠለቁ ሲሆን እንደየቀለማቱ ቅደም ተከተል አንደኛ፣ ኹለተኛ፣ ሦስተኛ እና አራተኛ አገር በቀል ባታሊዮን የሚል መጠሪያ ተሰጥቷቸው ነበር።






የጣሊያን ጦር ከምፅዋ በመነሳት ወደ ደጋማው የኢትዮጵያ ክፍል መንቀሳቀስ ሲጀምር ተጨማሪ ወታደር አስፈልጎት ነበር። አራት ተጨማሪ ባታሊዮን በመመልመል በአጠቃላይ እያንዳንዱ አንድ ሺህ አባል ያለው ስምንት የባንዳ ባታሊዮን ማዋቀር ቻለች። አዳዲሶቹ ባታሊዮኖች ባለ መስቀለኛ የስኮትላንድ መታጠቂያ እንዲሁም አረንጓዴ፣ ነጭ እና ቢጫ ቀለማት ያሏቸውን ቀበቶዎች እንዲታጠቁ ተደረጉ።

በጥንታዊ የኦቶማን አጠራር «ባሺ-ቡዙቅ» ወይም «አስካሪ» የሚል ስያሜ የተሰጣቸው አዳዲሶቹ ምልምሎች በነጭ ወታደራዊ ዩኒፎርሞቻቸው ይታወቁ ነበር። ወንጀል ሠርተው በመሸሽ ላይ የነበሩ እንዲሁም የባሪያ ንግድን በመሸሽ ላይ የነበሩ ሰዎች የአስካሪ ውትድርናውን በየጊዜው መቀላቀል ቀጠሉ። በውትድርና የምግብ፣ የልብስ እና የገንዘብ ዋስትናን ማረጋገጫ ተደርጎ ስለሚታይ በርካቶች የጣሊያንን ምልምል ጦር ተቀላቀሉ።



Askari recruits. From L'Illustration, 21 December 1895.

ምስል፦ የአስካሪ (ባንዳ) ምልምል ወታደሮች (ላ ኢሉስትራሽን - ታኅሳስ 21 ቀን 1895)



Askari recruits. From *L'Illustration*, 21 December 1895.

ምስል፡- የአስካሪ (ባንዳ) ምልምል ወታደሮች (ላ ኢሉስትራሽን - ታኅሳስ 21 ቀን 1895)

አንድ አስካሪ ምልምል የአንድ ዓመት ኮንትራት ከፈረመ በምላሹ የሚያገኘው የቀን ክፍያ አንድ የጣሊያን ሊሬ ከአምሳ ሳንቲም ነበር። ከአውሮፓውያን ወታደሮች ክፍያ አንፃር ሲታይ አነስተኛ ቢመስልም በዘመኑ ለአንድ አፍሪካዊ ወታደር ትልቅ ዋጋ ነበረው። አንድ አስካሪ ወታደር በክፍያው በቂ ኑሮ መምራት የሚችል ሲሆን ሚስት አግብቶ ቤተሰብ መመስረትም ሆነ ከአንድ ዓመት በኋላ የግል በቅሎ መግዛት ያስችለዋል።

የውትድርና ሥራው ከሚያስገኘው ገቢ በላይ ለተቀጣሪዎች የክብሬታ ምንጭም ሆኖላቸው ነበር። በመላው ምሥራቅ አፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ወታደር የተለየ ክብር ይሰጠዋል። ቅጥረኛ ወታደሮቹ ለአንድ ዓመት ካገለገሉ በኋላ የሚያገኙት ክፍያ ከግብርና የተሻለ ኑሮ እንዲመሩ ያስችላቸዋል። በዘመኑ ውትድርና የተሻለ ሕይወት አማራጭ ነበር።

በአስካሪ ምልመላው ጣሊያን ዜጎቿም ባይኾኑ ለጥቅሟ የሚዋጉ ቆራጥ እና ቀልጣፋ ወታደሮችን መመልመል ችላለች። ቅጥረኞቹ ለአውሮፓውያን ወታደሮች አስቸጋሪ በኾኑት የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ደጋማ ቦታዎች ላይ በተሻለ ብቃት መሰለፍ ችለዋል። ከስድስት ሺህ ጫማ በላይ ከፍታ ያላቸው ተራሮች ላይ ለመንቀሳቀስ የሞከሩ የአውሮፓ ወታደሮች ብርዱን መቋቋም ሲሳናቸው የአገሬው ቅጥረኛ ግን በአስገራሚ ጥንካሬ ይጓዝ ነበር።

አስመራ የነበረው ፖል ላሪባር በእዙ ሥር የነበሩትን ቅጥረኛ ወታደሮች በመያዝ ከአስመራ በ118 ማይል ርቀት ወደምትገኘው አቆርዳት እንዲንቀሳቀስ በታዘዘ ወቅት በስሩ የነበሩት ቅጥረኛ አስካሪዎች ርቀቱን ለመጨረስ የወሰደባቸው ጊዜ ሦስት ቀናት ብቻ ነበር። ይህም ማለት በቀን (በዐሥራ ኹለት ሰዓት) ከሠላሳ ማይል በላይ መጓዛቸውን ያሳያል። በአውሮፓውያን ዘንድ በፈጣን ተጓዥነታቸው የሚታወቁት የናፖሊዮን ወታደሮች በቀን መጓዝ የቻሉት ርቀት ከሐያ አምስት ማይል ያልበለጠ ነበር።





የአስካሪ ቅጥረኞቹ ፈጣን የመጓዝ ችሎታ የጣሊያን ሠራዊት ከኢትዮጵያ ባላንጣው ጋር እንዲስተካከል ዕድል ፈጥሮለታል። በ1895ቱ ወታደራዊ ዘመቻ ወቅት እንደታየው በመሸሽ ላይ ለነበረ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሳይቀር ፈታኝ የነበረው ከጣሊያን ጎን የተሰለፉት ቅጥረኞች ፍጥነት ነበር። አስካሪ ቅጥረኞቹን ባያሰልፉ ኖሮ ጣሊያኖች የኢትዮጵያን ሠራዊት ፈጣን ግስጋሴ መገዳደር ያስቸግራቸው ነበር።

አስካሪ ወታደሮች በአውሮፓውያን መኮንኖች እዝ ሥር የነበሩ ቢሆንም አንዳንድ ልዩ ብቃት ያሳዩ አስካሪዎች መካከለኛ ወታደራዊ ማዕረግ ይሰጣቸው ነበር። የደረጃ ዕድገት ያገኙ ቅጥረኞች በቀይ ወታደራዊ ቆባቸው ላይ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ጨርቆች ያስሩ ነበር።

የቅጥረኞቹ መኖር ለጣሊያን ወታደራዊ መኮንኖች ከፍተኛ እረፍት እና መዝናናትን ፈጠረላቸው። የጣሊያን መኮንኖችም የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች የነበራቸውን ክብሬታ ማግኘት ቻሉ። የየዕለቱ ዘመቻ በተጠናቀቀ ቁጥር የቅጥረኞች ቀጣይ ሥራ የነበረው ለጣሊያናውያን መሪዎቻቸው ማረፊያ ዳስ እና ድንኳን መጣል ነበር። በተጨማሪም አለቆቻቸውን በግል ጠባቂነትም ያጅቡ ነበር። የአንዳንድ መንደሮች ነዋሪዎች ለጣሊያን ወታደሮች እንዲያቀርቡ የሚገደዱት ምግብ ለጣሊያናውያን አለቆቻቸው የሚመጥን ጣዕም እንዳለው እንዲሁም ያልተመረዘ መኾኑን ለማረጋገጥ ቀድመው ይቀምሱት የነበሩት ቅጥረኛ አስካሪዎቹ ነበሩ።

ለቀጣሪዎቻቸው ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ ሲሉ በወገኖቻቸው ላይ እርምጃ የሚወስዱ አንዳንድ አስካሪዎችም ታይተዋል። በአንድ ባታሊዮን ሥር የሚገኙ ቅጥረኞች እርስ በእርሳቸው የሚጠቃቁበት አጋጣሚ የታየ ሲሆን በአብዛኛው ግን በመካከላቸው ልዩ መግባባት ይታይ ነበር።

የጣሊያን ወታደራዊ ባህል ከሌላ አውሮፓውያን ልዩ የሚያደርገው ቤተሰባዊ ተሳትፎን መፍቀዱ ነበር። የጣሊያን ወታደሮች ሚስት እና ልጆቻቸውን አስከትለው እንዲዘምቱ በመፍቀድ ዘመቻውን ቤተሰባዊ ለማድረግም ችላለች። የቅጥረኛው ወታደር ሚስት እና ልጆች የዘመቻው አጋዥ የኾኑበት አጋጣሚ በተደጋጋሚ የታየ ሲሆን በተለይም መቀሌ ላይ በተደረገው ጦርነት ጥይት እና በምብ የማቀበል ኃላፊነት ላይ ተሰማርተው የነበሩት የአስካሪ ሚስቶች እና ወጣት ልጆች ናቸው።

የጣሊያን ወታደራዊ መሪዎችን ያስገረሙ አንዳንድ ኹነቶችም ተስተውለው ነበር። አስካሪ ወታደሮች በምሽግ ቁፋሮ ወቅት የጣሊያን ወታደራዊ መዝሙሮችን ይዘምሩ ነበር። ከበርካታ የጣሊያን መኮንኖች የጉዞ ማስታወሻዎች ላይ እንደታየው መኮንኖች ለአስካሪዎቹ ታማኝነት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

በርካታ አስካሪዎች የጣሊያንን ቋንቋ እና ባህላዊ ሁኔታ ለመልመድ ይሞክሩ ነበር። ቁጥሩ ከ3600 በላይ ከሚገመተው ቅጥረኛ ሠራዊት መካከል ከግማሽ በላይ የሚኾኑት የጣሊያንን ቋንቋም ሆነ ወታደራዊ ትዕዛዝ አይረዱም ነበር። በአንድ ወቅት ጣሊያናዊው ጀነራል አንቶኒዮ ባልዲሴራ ቅጥረኞችን ከጣሊናውያን ጎን ለማሳለፍ የነደፈውን ሀሳብ ሮም ውድቅ አድርጋበታለች። ይህ የሚያሳየው የወቅቱ የጣሊያን ጦር አሰላለፍ የነጮች የበላይ አለቃነት ላይ ያተኮረ እንደነበር ነው።

በምልመላ ወቅት ጣሊያን ኃይማኖታዊ መስፈርትን ባለመጠቀሟ የተነሣ ሙስሊም እና ክርስቲያን አስካሪዎችን መልምላ ነበር። የተለያየ ኃይማኖት ቢኖራቸውም በቅጥረኞቹ መካከል ፍጹማዊ መግባባት ነበር። ለምሳሌ ያህል ጣሊያኖች ያቀርቡላቸው የነበረውን ሥጋ ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ ቅጥረኛ በአንድ ላይ ይመገቡ ነበር።





## ፍቅር በአፍሪካ

አስካሪ ወታደሮች በወታደራዊ ዘመቻው ወቅት የግላዊ ሕይወት ግንኙነት የማድረግ ነጻነት ነበራቸው። በመኾኑም ሚስቶቻቸውን ይዘው ይዘዋወሩ ነበር። የጣሊያን ወታደሮች ግን በአንፃሩ የወታደራዊ ደንቡ ይህንን እንዳያደርጉ ያግዳቸው ነበር። በ1895 ማብቂያ አካባቢ ቁጥራቸው ወደ ዐሥር ሺህ የሚገመት የጣሊያን ወታደሮች በኢትዮጵያ የተሰማሩ ቢሆንም ከከፍተኛ መኮንኖች ውጪ ሚስቶቻቸውን አስከትለው እንዲዘምቱ አይፈቀድላቸውም ነበር። የአጠቃላይ ጦሩ ምክትል አዛዥ የነበረው መኮንን ብቻ ሮዛሊያ ፒያናዚያ የተባለች ሚስቱን አስከትሎ አስመራ እንደመጣ ይታወሳል።

በዘመቻው ወቅት አውሮፓውያኑ ምን ያህል በወሲብ እንደተፈተኑ ማሰብ ቢቻልም የነበረውን እውነታ ግን መዘገብ አስቸጋሪ ነበር። የበርካታ ወታደሮች የጉዞ ማስታወሻ ከወሲብ ጋር ተያያዥ የነበሩ እውነታዎች አድበስብሰው ያለፉት ቢሆንም አንድ ጭምጭምታ መኖሩን ግን በተለያዩ አጋጣሚዎች ለመስማት ተችሏል። ይኸውም ፊኒዮሉ የተባለ አንድ የጣሊያን ወታደር በወታደራዊ ካምፑ አካባቢ ‹‹ወይዘሪት›› ተብሎ ይታወቅ እንደነበር ነው።

ጣሊያናውያኑ በ1936 ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲዘምቱ የጣሊያን ዘርን ክብር እንዲጠብቁ የሚያስገድዱ በርካታ ደንቦች ተጥለውባቸው ነበር። በ1880ዎቹ ግን አስገዳጅ ደንቦች አልነበሩም። እንደማንኛውም የወደብ ከተማ በምፅዋ ሴተኛ አዳሪዎች የነበሩ ሲሆን፤ በአስመራና በተለያዩ ከተሞች የነበሩ የጣሊያን ጦር ሠራዊት አባላት ሴተኛ አዳሪዎችን ከመጎብኘት ይልቅ ከኤርትራዊ ሴቶች ጋር ትዳር መሰል ግንኙነትን መመስረት መርጠው ታይተዋል። የጣሊያናውያኑ ቅምጥ የነበሩ እንስቶች ‹‹ማዳማ›› በሚል የማዕረግ ስማቸው ይጠሩም ነበር። ጀነራል ጁሴፔ አሪሞንዲ ውበቷ ወደር የሌለው ኤርትራዊት አግብቶ እንደነበር እና አድዋ ላይ ከመሞቱ በፊትም አብሯት ይኖር እንደነበር ይታወሳል።

በጣሊያን ወታደሮች እና በኤርትራ ወይዛዝርት መካከል የነበረው የፍቅር ግንኙነት የትዳር ያህል ጥብቀት የነበረው ቢሆንም አንዳንድ መገራበጦች ግን ይስተዋሉበት ነበር። ሲዛር ኔራዚኒ በኤርትራ የጣሊያን ልዩ መልዕክተኛ በነበረባቸው ዓመታት ከአንዲት ኤትራዊት ጋር ፍቅር መሥርቶ አሰብ ይኖር ነበር። የሚገርመው ታዲያ ኔራዚኒም ሆነ ፍቅረኛው የየራሳቸው ፍቅረኞች ነበሯቸው። ኔራዚኒ ምጣ ከተባለች ሴት ፍቅር ያዘውና ከመጀመሪያዋ ፍቅረኛው መኖሪያ አጠገብ ቤት ተከራይቶ ሲያስቀምጣት ፍቅረኛው በበኩሏ ሮዜንትሬተር ከተባለ የስዊዝ መካኒክ ጋር ግንኙነት ጀመረች።

በአንዳንድ አጋጣሚዎች እንደታየው የፍቅር ግንኙነቶች ወደ ሕጋዊ ጋብቻ ማደግ የቻሉበትም አጋጣሚ ነበር። ክሪስ ፕሮቲ በማስታወሻዋ እንደገለጸችው የአገሬው ሰዎች ሴት ልጆቻቸውን ለአውሮፓዊ ወታደሮች ለመዳር የተለየ ጥረት ያደርጉ ነበር። የጣሊያን ወታደሮች በጥሎሽ መልክ የተሟላ ቤት፣ እህል እና ጥሬ ገንዘብ ይከፍሉ ነበር። የልጃገረድ አባት የተዋበ ሰጋር በቅሉ በስጦታ መልክ ያገኝ ነበር። ልጅቷም ጣሊያናዊ በማግባቷ «ማዳማ» የሚለውን የማዕረግ ስም በማግኘት ከሌሎች የተለየ ክበሬታን ታገኛለች። በርካታ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለአውሮፓውያን በመዳር አፍሪካዊ ዘራቸውን ከነጭ ጋር ማዳቀል መቻላቸውን እንደተለየ ክብር ያዩት ነበር።

የአንድ ጣሊያናዊ እጮኛ የሆነች «ማዳማ» ባለቤቷ ወደ አውሮፓ ከተመለሰም በኋላ ማዕረጓን ይዛ ትቆያለች። በትዳር ወቅት ያካበተችውን ሐብት እና ዝና በመጠቀምም ሌላ አውሮፓዊ ወይም የአገሯን ሰው ማግባት ትችላለች።

በዚህ መሰል የፍቅር ግንኙነት የሚወለዱ ክልስ ልጆች በማህበረሰቡ ተቀባይነት እና ክበሬታን ለማግኘት ይቸገራሉ። ከወራሪው የናዚ ወታደር እንደተወለደ ፈረንሳዊ ሕፃን ልጅ ኹሉ ማህበረሰቡ ህፃኑን ኤርትራዊ እንደ ወራሪ ጣሊያናዊ





ይመለከት ነበር። ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ ግን ክልስ ልጆች በኤርትራዊያን ተቀባይነት ማግኘት የቻሉ ሲሆን አንዳንዴም የተሻለ ክብር ይሰጣቸው ነበር።



ምስል፦ ጣሊያናዊ ወታደር ከኤርትራዊት ባለቤቱ ጋር

በኢትዮጵያ ተመሳሳይ የነጭ እና ጥቁር ጋብቻዎች እንደነበሩ የሚጠቁሙ ነገሮች ይታዩ ነበር። አጉስተስ ዋይልድ የጣሊያን እና ኢትዮጵያን ስምምነት ሐተታ ለ«ማንቼስተር ጋርዲያን» ጋዜጣ ለመዘገብ ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ወቅት አንዲት ነጭ ሴት አግኝቶ ነበር። ሴቷ በ1868ቱ የናፒየር ዘመቻ ወቅት ከእንግሊዝ ወታደር እና ኢትዮጵያዊት እንስት የተወለደች ስትሆን በአካባቢው ነዋሪ «እንግሊዟ» በሚል ስሟ ነበር የምትታወቀው። ዋይልድ ባገኛት ወቅት እንስቷ ከኢትዮጵያ ወንድ ጋር ከመሰረተችው ትዳር አንዲት ሴት ልጅ ወልዳ ነበር።



Italian sol[illegible] Ma[illegible] From SAI Archive at the University of Naples
L'Orientale [illegible] Palma, *Archivio storico della Società africana d'Italia:*
[illegible] Napoli [illegible] Orientale [illegible]

በተለያዩ የምሥራቅ አፍሪካ ቦታዎች በተለይም በኤርትራ ከጣሊያን አባት የተወለዱ ክልስ ልጆችን ማየት የተለመደ ሲሆን ማህበረሰቡም ቀስ በቀስ ክልሶቹን መቀበል ጀምሮ ነበር። ጣሊያናዊው ሜጀር ጀነራል ፒየትሮ ቶሴሊ በ1895ቱ ዘመቻ ወቅት ሲሞት ከኤርትራዊት ሚስቱ የወለደው ወንድ ልጅ ነበረው። ኤርትራዊቷ ሌላ ባል ስታገባ አዲሱ ባሏ ክልስ እንጀራ ልጁን ተቀብሉ ማሳደግ የቻለ ሲሆን ለሚች የሥጋ አባቱ መታሰቢያ እንዲሆንም ክልሱን ጴጥሮስ በማለት ሰይመውት ነበር።

የበርካታ ክልስ ልጆች አባቶች በጦርነት ወቅት ሲሞቱ እንዲሁም ግዴታቸውን አጠናቀው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ልጆቹ ያለ አባት ይቀሩ ነበር። ሮዛሊያ ፒያናቪያ የተባለችው የአንድ ጣሊያናዊት መኮንን ሚስት በርካታ አባት አልባ ክልስ ሕፃናትን ሰብስባ ትረዳ እንደነበር ይታወሳል። «አባዲ» የተባለች ክልስ ሕፃን ኤርትራዊት እናቷ ከሞተችባት እና አባቷም ወደ አገሩ ጣሊያን ከተመለሰ በኋላ በአደራ የተቀበለቻት ፒያናቪያ ነበረች። «አባዲ» የሚለውን ስም «ማሪያኒያ» በሚል ከቀየረችላት በኋላ የማሳደግ ኃላፊነቱን መወጣት ጀመረች።

የወቅቱን የቅኝ ግዛት አስተዳደር በማስፈቀድ የመጀመሪያውን የወላጅ አልባ ሕፃናት መንደርም ለመገንባት ቻለች። አስተዳደሩ የመንደሩ መገንባት የወታደሩን ወሲባዊ ተግባር በማበረታታት ችግር ሊፈጥር ይችላል በማለት መጀመሪያ ላይ ቢቃወምም በኋላ ግን ፈቀደላት። ማሪያኒያ የመጀመሪያዋ የማዕከሉ ልጅ ስትሆን በመቀጠል መንደሩን አንጀሊና፣ ቪቶሪያ፣ ሊቺኖ፣ አሬስቲ እና ጂዮቫኒኖ የተባሉ ወላጅ አልባ ክልስ ሕፃናት ተቀላቀሉ።

የሮዛሊያ እንቅስቃሴ በመጠናከር በአስመራም ተመሳሳይ መንደር ለመገንባት ቻለች። በአስመራ እና በጣሊያኗ ከተማ ጀኖላ ተመሳሳይ የነበሩ የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶችን በማድረግም የወላጅ አልባ ክልሶቹን ማዕከላት የበለጠ አጠናከረቻቸው። ከ28 ሺህ ሊሬ በላይ ገንዘብ በማሰባሰብም በርካታ ሞግዚቶችንና መምህራንን በማዕከሉ ቀጠረች። በመቀጠል በርካታ የካቶሊክ መነኮሳት ማዕከሉን በመምህርነት ለመደገፍ ከጣሊያን ድረስ መጡ።





የፒያናቪያ ሕፃናት ማዕከል የወላጅ አልባ ሕፃናቱን ሕይወት የመታደግ ተግባር ቢፈጽምም የአውሮፓውያኑ እና አፍሪካውያኑ የፍቅር ግንኙነት እንዲሁም የአስካሪ ቅጥረኛ ወታደሮች ተሳትፎ በኹለቱ ሕዝቦች መካከል መተሳሰርን ለመፍጠር የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል። ማዳማዎች እና አስካሪዎች በሚያገኙት የገንዘብ እና የደረጃ ክብር በመገፋፋት ከጣሊያውያኑ ጋር ቁርኝታቸውን በማጥበቅ ለቅኝ ገዢዎች ቀይታ የተሻለ ሁኔታን ፈጥረዋል።